አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በደብረ ታቦር ከተማ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ትኩረት ዘዴ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት፡ በ፰ኛ ክፍል ተተኳሪነት


በ
ሶስና አበቀ



[illegible]
[illegible] አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ
አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በደብረታቦር ከተማ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ዘዴ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት፤ በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት።

በ

ሶስና አወቀ

መጋቢት 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በደብረታቦር ከተማ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ዘዴ አተገባበር

ንጽጽራዊ ጥናት፤ በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት።

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ
# አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
# የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር /ALTA/ ኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
ሶስና አወቀ

መጋቢት 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ
# አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
# የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

## በደብረታቦር ከተማ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ዘዴ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት፤ በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት።


በ

ሶስና አወቀ


መጋቢት 2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ደክመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይህ ጥናት ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ድረስ በስኬት እዲጠናቀቅ እርማት በመስጠትና ትክክለኛውን አቅጣጫ በማስያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ ለመምህሬና አማካሪየ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናየ ከልብ ነው!

የትምህርት ወጪየንና ደመወዜን በመክፈል ላስተማረኝ ለአማራ ክልል ትምህርት ቢሮና አዲስ ዘመን መሰናዶ ትምህርት ቤት እንዲሁም የጥናት ወጪየን በመደገፍ ትብብር ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናየን ልገልጽ እወዳለሁ፡፡

ለዚህ ጥናት ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የዳግማዊ ቴዎድሮስ፣ ፊታአውራሪ ገብርየ፣ ዲቲ አካዳሚና ዳልሽህ ቤዛዊት አለም 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ትምህርቴንና ይህንን ጥናት ዳር ለማድረስ በሀሳብ፣ በገንዘብና በጉልበት ለደገፉኝና ከጎኔ ሆነው ምንጊዜም አይዞሽ ለሚሉኝ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ሁሉ ምስጋናየ ይድረሳቸው፡፡

# አበርክቶ

"ቋንቋየ" ቋንቋየ ህይወቴ ስኬቴ፣
እናትየ "ወርቂት" የእኔ ማንነቴ፡፡
እናትየ እናቴ ልጅሽ ደርሻለሁ፣
እንደ ዘወትር ፀሎት ሁሌ እደግምሻለሁ፣
አፈር መስኮት ኖሮት ባየሽኝ እላለሁ፣
ግን እናቴ "ወርቂት" የት አገኝሻለሁ፣
በፈጣሪ ስራ ምንስ አደርጋለሁ፡፡
እናትየ እውቃለሁ በርጅና ዘመንሽ፣
እኔን አሳደግሽኝ "አንቺ እንዳልሽ"፣
ብለሽ፣
ግን እናቴ "ወርቂት" ከእኔ ምን አገኘሽ፣
ፍሬሽን ባየሽው እንደዚያ እ"ደደከምሽ (2)፡፡
"ቋንቋየ" እወድሻለሁ! አሁንም እውድሻለሁ!
እናቴ እወድሻለሁ! ሁሌም እወድሻለሁ!
ግን ምን አደርጋለሁ? የት አገኝሻለሁ?
እኔም ቀኔ ሲደርስ ወደ አንቺ እመጣለሁ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ..... i
አበርክቶ ..... ii
ማውጫ ..... iii
የአባሪ ማውጫ ..... vi
የሰንጠረዥ ማውጫ ..... vii
አጠቃሎ ..... viii
ምዕራፍ አንድ
መግቢያ
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ..... 3
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3
1.4. የጥናቱ ወሰን ..... 4
ምዕራፍ ሁለት
የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት
2.1. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ምንነት ..... 5
2.2. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዓላማ ..... 6
2.3 የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ባህሪያት ..... 7
2.4. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ጠቀሜታ ..... 8
2.5. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ መርሆች ..... 9
2.6. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ሥነ-ትግበራ መንገዶች ..... 10
2.6.1. በራስ/በግል የመማር ዘዴ ..... 10
2.6.1.1. በራስ /በግል/ የመማር ዘዴ ምንነት ..... 10
2.6.1.2. በራስ የመማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ..... 11
2.6.2. በቡድን የማስተማር ዘዴ ..... 12
2.6.2.1. በቡድን የማስተማር ዘዴ ምንነት ..... 12
2.6.2.2. የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠቀሜታ ..... 13

2.6.2.3. የቡድን ማደራጃ መንገዶች ...... 14
2.6.2.4. የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ...... 15
2.6.3. ችግር ፈች የማስተማር ዘዴ ...... 16
2.6.3.1. የችግር ፈች ማስተማር ዘዴ ምንነት ...... 16
2.6.3.2. የችግር ፈች ማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ...... 17
2.6.4. የሚና ጨዋታ ዘዴ ...... 17
2.6.4.1. የሚና ጨዋታ ዘዴ ምንነት ...... 17
2.6.4.2. በሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ...... 18
2.6.5. በፕሮጀክት ሥራ የማስተማር ዘዴ ...... 19
2.6.5.1. በፕሮጀክት ሥራ የማስተማር ዘዴ ምንነት ...... 19
2.6.5.2. የፕሮጀክት ሥራ የማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ...... 19
2.7. በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የመምህሩና የተማሪው ሚና ...... 20
2.7.1. የመምህሩ ሚና ...... 20
2.7.2. የተማሪው ሚና ...... 21
2.8. በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ...... 22
2.8.1. የለውጡ ባህሪይ ...... 22
2.8.2. የመምህራን አመለካከት ...... 22
2.8.3. ለመምህራን የሥራ ላይ ስልጠና አለመስጠት ...... 22
2.8.4. ለተማሪዎች ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና አለመስጠት ...... 22
2.8.5. ለተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ መሳሪያዎች አመች አለመሆን ...... 22
2.8.6. የመማሪያ ክፍሎችና የተማሪዎች ቁጥር አለመመጣጠን ...... 24
2.8.7. አካባቢና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ...... 24
2.8.8. በቂ ጊዜ አለመኖር ...... 24
2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት ...... 25
ምዕራፍ ሶስት
የአጠናን ዘዴ
3.1. የናሙና አመራረጥ ...... 27

3.1.1. የክልል አመራረጥ ........................................ 27
3.1.2. የትምህርት ቤት አመራረጥ ........................................ 27
3.1.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........................................ 28
3.1.4. የመምህራን አመራረጥ ........................................ 28
3.1.5. የተማሪዎች አመራረጥ ........................................ 28
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................ 30
3.2.1. ምልከታ ........................................ 30
3.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ ........................................ 31
3.2.3. ቃለ መጠይቅ ........................................ 32
3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................ 32
ምዕራፍ አራት
የመረጃ ትንተና
4.1. የተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ ........................................ 34
4.2. በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የመምህሩ ተግባር (ሚና) ........................................ 36
4.2.1. በተማሪ ተኮር ትምህርት መግቢያ የመምህራን ሚና ........................................ 36
4.2.2. በትምህርቱ ሂደት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሚና ........................................ 38
4.2.3. የመምህሩ የተማሪ ተኮር ትምህርት ስነ-ዘዴ አተገባበር ........................................ 40
4.3. በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ (ሚና) ........................................ 43
4.4. ትምህርት ቤቱና የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው ምቹነት ........................................ 46
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና አስተያየት
5.1. ማጠቃለያ ........................................ 49
5.2. አስተያየት ........................................ 53
ዋቢ ጽሑፎች ........................................ 54
ሙዳየ ቃላት ........................................ 59
አባሪዎች ........................................ 60

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ሠንጠረዥ 1 የተመረጡ ተማሪዎች ዳራ ..................... 29

ሠንጠረዥ 2 የተጠኘ መምህራን ዳራ ..................... 34

ሠንጠረዥ 3 ለጥናቱ መረጃ የሰጡ (የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ) ተማሪዎች ዳራ ..................... 35

ሠንጠረዥ 4 በትምህርት መግቢያ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት ..................... 36

ሠንጠረዥ 5 በትምህርት ሂደቱ የመምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት ..................... 38

ሠንጠረዥ 6 የመምህሩ የተማሪ ተኮር ትምህርት የስነ ዘዴ አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት ..................... 40

ሠንጠረዥ 7 በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተማሪዎች ሚና (ተሳትፎ) የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት ..................... 44

ሠንጠረዥ 8 ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ትምህርት ቤቱና የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው ምቹነት የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት ..................... 46

ሠንጠረዥ 9 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት ..................... 47

# የአባሪ ማውጫ

ርዕስ ገጽ


አባሪ1 ሥራ ላይ የዋሉ የቲ-ቴስት ስሌት ቀመሮች....................61

አባሪ 2 በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ....................63

አባሪ 3 የምልከታ ማመሳከሪያ ሰነድ /ቅጽ/....................64

አባሪ 4 ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ....................66

አባሪ 5 ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ....................70

አባሪ 6 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ....................71

አባሪ 7 ከምልከታና ቪዲዮ ቀረጻ የተገኘ መረጃ....................75

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረ ታቦር ከተማ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽና ማነጻጸር ነው። የጥናቱን ተተኳሪዎች ለመምረጥም የአመችና ጠቅላይ ናሙናን ተጠቅሟል። ከነዚህ ተተኳሪዎችም በቪዲዮ ቀረጻና ረዳት መረጃ ሰብሳቢ በታገዘና በተደራጀ ምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም በቃለመጠይቅ አማካኝነት መረጃ ተሰብስቧል። በዚህ መሠረትም የተሰበሰበው መረጃ የአይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ በገለፃ ስልት ተተንትኗል። በትንተናውም የቲ-ቴስት ስታስቲካዊ ስሌት ስራ ላይ ውሏል። የስታስቲክስ ስሌቱም አማካይ ውጤት፣ ልይይትና የነጻነት ደረጃን በግብዓትነት ተጠቅሟል። በዚህ ሁኔታም የተገኘው አጠቃላይ አማካይ ውጤት የግል ትምህርት ቤቶች በምልከታ 3.717፣ በጽሑፍ መጠይቅ 4.249 ሲያስመዘግቡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ደግሞ በምልከታ 3.575፣ በጽሑፍ መጠይቅ 3.955 አግኝተዋል። በመሆኑም በምልከታ የተገኘው የቲ ቴስት ውጤት 0.087 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋው 4.303፣ በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ የቲ-ቴስት ውጤት 0.505 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.960፣ በመሆኑና በሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያዎች አማካኝነት የተገኙ የቲ-ቴስት ውጤቶች ከቲ-ስንጠረዥ ዋጋቸው ያነሱ በመሆናቸው በአማካይ ውጤታቸው የግል ትምህርት ቤቶች በመጠኑ የተሻሉ ሆነው ቢታዩም በቲ-ቴስት ውጤቱ ግን ጉልህ ልዩነት እንዳልተፈጠረ ተረጋግጧል። ይሁን እንጂ በምልከታው ለማረጋገጥ እንደተሞከረው የግል ትምህርት ቤቶችም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከግል እና ከቡድን የተማሪ ተኮር ትምህርት መተግበሪያ መንገዶች (ስነ-ዘዴዎች) ውጭ ሌሎችን ማለትም ችግር ፈች፣ የፕሮጀክትና የሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴዎችን ተግባራዊ እንደማያደርጉ ተረጋግጧል። ለዚህም ምክንያቱ የትምህርት ቤቶች የትምህርት ግብዓት አቅርቦትና የመማሪያ ክፍሎች ችግር እንዲሁም የመምህራን የሥራ ላይ ስልጠና አለማግኘትና አጥጋቢ አለመሆን ወዘተ. ጉዳዮች እንደሆኑም ለመገንዘብ ተችሏል። ስለሆነም በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ለማምጣት ያስችል ዘንድ ጥናቱ የመፍትሄ ሀሳቦችን ጠቁሟል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ምሁራን በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራንና ተማሪዎችን ተሳትፎ ከግንዛቤ በማስገባት የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንደሚከተለዉ ከፍለዋቸዋል። Borich (1988) እንደገለጹት የትምህርት ዋና አላማ የተማሪዎችን እውቀት፣ ክሂሎት እና አመለካከት ማሳደግ ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን መተግበር ይገባል። ምክንያቱም የትምህርት ውጤታማነት ከማስተማሪያ ስነ-ዘዴው ጋር የተቆራኘ ነው። በመሆኑም መደበኛው የማስተማሪያ ዘዴ ሁለት ዋና ዋና አቀራረቦች አሉት። አንደኛው ዘዴ በመምህር መራሽ ሲሆን በዚህ ጊዜ የመምህሩ ሚና እውነታን (Facts)፣ መመሪያን (rules)ና የተግባራትን ቅደም ተከተል (actions sequence) ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ ነዉ። በዚህ ዘዴ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ማንነት በውል የማያውቁበትና ተማሪዎች ምን ተማሩ (አወቁ) ከማለት ይልቅ ምን አስተማርኩ (what is taught) በማለት የትምህርት ይዘቱን ለመሸፈን የሚፋጠኑበት ስነ-ዘዴ ነው።

ሌላኛው ዘዴ ደግሞ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ነው። ይህ ዘዴ ትኩረቱን በተማሪዎች ላይ በማድረግ የመማር ማስተማሩን ሂደት በማቀድ (conceived) በመተግበር (executed) እና በመመዘን (evaluated) የተማሪዎችን ፍላጎት ማዕከል አድርጎ ዓላማዉን ማሳካት መቻል ነው በማለት ገልጸዋል።

መምህር መራሽ የትምህርት አቀራረብ ትኩረቱን መምህራን ለተማሪዎቻቸዉ በሚያስተላልፉት እውቀት (ትምህርት) ላይ የሚያደርግ ሲሆን የተማሪ ተኮር ትምህርት ደግሞ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት የሚመሠረትና ተማሪዎች በራሳቸው ችግር ፈቺ እንዲሆኑ የሚረዳ መሆኑን Aggrarwal(1996) ገልጸዋል።

በተጨማሪም መደበኛው የመምህር መራሽ ትምህርት የሚካሄደው በመምህራን ተዋናይነት ነበር። ይሁን እንጂ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዋና ተግባሩ የትምህርት ተዋናይነቱን ከመምህራን ወደ ተማሪዎች በማሸጋገር መምህራንን አመቻች ተማሪዎችን ደግሞ ተዋናይ አድርጎ የተቀላጠፈ ተስተምሮ እንዲፈጠር ማስቻል ነው Lue (2000)።

በሌላ በኩል ደግሞ Larmar (1978) በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የመማር ነፃነታቸው ተጠብቆላቸው ምን፣ መቼ፣የትና እንዴት መማር እንደሚፈልጉ በመረዳት ተገቢውን አተገባበር ተከትሎ ትምህርትን ውጤታማ ማድረግ ነዉ። ይሁን እንጂ በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው ይህ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ በተገቢው መንገድ ሲተገበር አይስተዋልም።በጥናቶቹም የተገኘው መረጃ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች (materials) አለመሟላት፣ የተማሪዎች ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት ጠቀሜታ ጠንቅቀዉ አለማወቅና የመሳሰሉትን ችግሮች በምክንያትነት በመጥቀስ በትግበራው ላይ ክፍተት እንደሚታይበት ገልጸዋል።

እንደምሁራኑ ገለፃም ምንም እንኳን የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የአተገባበር ችግር ቢታይበትም ከመምህር መራሹ የማስተማር ዘዴ የተሻለና ውጤታማ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ በሀገራችንም ተግባር ላይ እየዋለ ያለ ዘዴ እንደሆነ ትምህርት ሚኒስቴር (1994) ይገልፃል። ይሁንእንጂ አተገባበሩ ችግር እንደሚታይበት ኢልያስ (1997)፣ሙሉጌታ (1996)ና ደረጀ (1999) በጥናታቸው ገልጸዋል።

በመሆኑም ይህንን ጥናት (ችግር) ለማጥናት እንደ አነሳሽ ምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮችም አንደኛ የቀደምት ስራዎች አሰሳ በሚካሄድበት ጊዜ በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተሰሩ ሁሉም ስራዎች በከሌጅ ደረጃ እንጅ በአንደኛ ደረጃ በተለይም የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ማዕከል ያደረገ ጥናት አለመኖርና ሁለተኛ እንዲህ ዓይነቱ ጥናትበአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ቢካሄድ ጠቃሚና የተለየ ዉጤት ይመጣል የሚል እምነት መኖር ናቸዉ።

ስለሆነም በዚህ ጥናት የሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመለሳሉ።

- በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር በምን ይመሳሰላል? በምንስ ይለያያሉ ?
- የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የሚታየው በየትኛው ትምህርት ቤት ነው? ለምን?

- ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች አሉ? ካሉስ ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይወገዳሉ?

የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የሚገኘውንም ምላሽ በተጨባጭ እውነታ አስደግፎ የመፍትሄ ሀሳቦችን ይጠቁማል።

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረ ታቦር ከተማ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽና ማነጻጸር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዘውም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ፣
- በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ረገድ በትምህርት ቤቶች መካከል ያለዉን ተመሳሳይነትና ልዩነት መመርመር፣
- በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር አንዱ ትምህርት ቤት ከሌላው ትምህርት ቤት የሚሻልበት ሁኔታ ካለ ማየትና ምክንያቱንም ማረጋገጥ፣
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ እንደ ችግር የሚነሱ ጉዳዮችን መለየትና የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም የሚሉት ይገኙበታል።

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

- ለመምህራንና ለተማሪዎች ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ንደፈ ሀሳባዊ እውቀት ያስጨብጣል፣
- የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በማሳየት የመማር ማስተማሩን ሂደት ያፋጥናል፣
- በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ስላለው የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር መረጃ ይሰጣል፣
- ወደፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ በስፋው ማጥናት ለሚፈልግ አካል መነሻ ሀሳብ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ትኩረት በደብረታቦር ከተማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽና ማነፃፀር ነው፡፡ ስለሆነም በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ 8ኛ ክፍልን በሚያስተምሩ በሁለት የግልና በሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን የሚመለከት ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉ ጉዳዮችን ግን አያካትትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ምንነት

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የተጀመረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በችኮዝላባኪያ ምሁራን ነው በማለት Amanu (2005፣22) ገልፀዋል። ይሁን እንጂ ይህ አቀራረብ በስፋት እየታወቀና ተቀባይነትን እያገኘ የመጣው በ1950 ዎቹ ገደማ እንደሆነ Wassihune (2006) ይገልጻሉ።

በተጨማሪም Sirak (2000)ና Terefe (2005) ይህ አቀራረብ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ያስቻሉት ምክንያቶችም፡-

- የተለያየ የመማር ስልት ያላቸውን ተማሪዎች ማዕከል ማድረጉ፣
- ከህብተሰቡ ጋር ተግባብቶ ለመኖር የሚያስችሉ ልምዶችን ለመቅሰም ማስቻሉና
- በተማሪዎች እውቀት፣ ፍላጎትና ስሜት ላይ የተመሰረተ ትምህርት ለማቅረብ ማስቻሉ መሆናቸውን ገልፀዋል።

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ምሁራን ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር በመመልከት የተለያዩ ስያሜዎችን ሰጥተውታል። ለአብነትም ICDR* (1999)፣ Burand (1999)ና Ginnis (1986) ኢ-ቀጥተኛ ዘዴ፣ ዘመናዊ፣ ኢ-ልማዳዊ በራስ የመማር ዘዴ፣ በትብብር የመማር ዘዴ ወዘተ. ብለዉታል። የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ከስያሜው እንደምንረዳው ትኩረቱን በተማሪዎች ላይ በማድረግ የትምህርት ዓላማን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል የትምህርት አቀራረብ ነው (Amanu 2005፣27)::

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ ተስተምሮ ሂደትን ማራኪ ለማድረግ ይረዳል። የመማር ማስተማሩ ሂደትም የተማሪዎችን የቀደመ እውቀትና የህይወት ልምድ መሰረት የሚያደርግ ነው። በመሆኑም በተማሪዎች ዘንድ መሰረታዊ የመማር ፍላጎትን እና የተረድኦት አቅምን ያጎለብታል። ስለሆነም ተማሪዎች የሚያገኙትን አዲስ ትምህርት ከቀድሞ እውቀታቸው ተነስተው ለመረዳትና ለማደራጀት እንዲሁም ማህበራዊ ህይወትን ለማጠናከር የሚያግዝ ነው (Tsegay 2001፣5)።

---

*ICDR-Institute of Curriculum Development and Research

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የተለያየ የመማር ስልት ያላቸውን ተማሪዎች ለመድረስ የሚያስችል ዘዴ ነው በማለት Siberman (1994፣4-5) ገልጸውታል።

በድሩ (1990፡9) ደግሞ በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪው ትምህርቱን በራሱ የመማር ፍላጎት፣ ስሜት፣ ተነሳስኦትና ጥረት እማካኝነት ያከናውናል።ስለሆነም ተማሪው ከመምህር ጥገኝነት ተላቅቆ ትምህርታዊ ተሳትፎውን በማሳደግ እውነተኛና ዘላቂ የሆነ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ያስችላል በማለት ገልጸዋል።

## 2.2. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዓላማ

በትምህርት ዓለም እያንዳንዱ እንቅስቃሴ፣ ይዘትና የማስተማሪያ ዘዴ ሁሉ ዓላማ አለው። በመሆኑም በድሩ (1990፡10) የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዓላማዎችን እንደሚከተለው አስፍረዋል።

- ተማሪውን በመማር ማስተማር ሂደት በሰፊው በማሳተፍ ለሚገጥሙት የተለያዩ ችግሮች በራሱ የመፍትሄ ሃሳቦችን እንዲያፈላልግ ማስቻል፣
- ተማሪው የትምህርት ሃላፊነቱን ተቀብሎ የመማር ስሜቱን በማሳደግ ተሳትፎው እንዲጨምር ማነሳሳት፣
- ተማሪው የሥራውን ውጤት በራሱ መመዘን የሚችልበትን አቅም ማዳበር ፣
- ተማሪው ወደፊት ሊገጥሙት ለሚችሉ ፈርጀ ብዙ ችግሮች ሳይንሳዊ የሆኑ መንገዶችን ለመጠቀም የሚያስችል ዝንባሌ፣ እውቀትና ክህሎትን እንዲያዳብር ማድረግ ናቸው።

በተጨማሪ Yalew (2004፡20) ደግሞ የተማሪ ተኮር ትምህርት ዓላማዎች፡-

- ተማሪው በራሱ ትምህርት ተሳታፊ እንዲሆን እድል መስጠት፣
- ተማሪው ለራሱና ለሌላው መማር የሃላፊነት ስሜትን እንዲያዳብር ማገዝ፣
- ለተማሪው የልምምድ ጊዜን በመስጠት ክህሎቱን በጋራ እንዲያዳብር ማድረግ፣
- የተማሪውን የማዳመጥ፣ የማሰብና ስርዓት ያለው ንግግር የማድረግ ክሂሎቱን ማሳደግ፣
- ተማሪው በተለያዩ ርዕሶችና ዕንስ ሃሳቦች ላይ የራሱን ግንዛቤ ማዳበር እንዲችል ማገዝና
- ተማሪው ችግር የመፍታት ክሂሉን እንዲያዳብር እድል መስጠት የሚሉት ይገኙበታል።

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዓላማ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲኖራቸውና የጥሩ ውጤት ባለቤት እንዲሆኑ ማስቻል ነው በማለት Tsegay (2001:4) ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዓብይ ዓላማው ተማሪዎችን በተሰለፉበት የትምህርት መስክ ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡ ውጤታማ ማድረግ ሲባልም በጥሩ ውጤት ወደሚቀጥለው ደረጃ ከመሸጋገር በተጨማሪም በተማሪዎች ላይ እውነተኛና ዘላቂ የሆነ የባህሪይ ለውጥ ማስገኘትን እንደሚያጠቃልል ከምሁራኑ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 2.3 የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ባህሪያት

በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በመወያየትና በመተባበር ትምህርታዊ ይዘቶችን የመምረጥ፣ የማዘጋጀት እና የምዘና ስልቶችን የመወሰን እድል አላቸው፡፡ ተማሪዎችን በእነዚህ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ማድረጉም የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማጠናከር የሚያግዙ ገንቢ ሀሳቦችን በማካተት የተሻለ የትምህርት ነሸ (Motivation) እንዲፈጠር ያደርጋል (Plass 1998፣310)፡፡

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ከዚህ የሚከተሉት ባህሪያት እንዳሉት Rogers (2002፣2)ና Temechegn (2002፣44) ይገልፃሉ፡፡

- ትምህርትን ከተግባር ጋር ማቀናጀት፣
- ለተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት የመምረጥና የመወሰን ነፃነት መስጠት፣
- የተማሪዎችን በራስ የመተማመን መንፈስን ማጎልበት፣
- ለተማሪዎች የመፍጠር፣ የመመራመርና ችግርን በራስ የመፍታት ልምድን ማስገኘት፣
- ትምህርቱን ከተማሪዎች የእለት ከእለት ተግባራት ጋር ማዛመድ፣
- የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ በማስገንዘብ የአስተሳሰብ አድማስን ማስፋት፣
- ተማሪዎችን ከፍዝ ተመልካችንት ወደ ንቁ ተሳታፊነት ማሸጋገር፣
- በተማሪዎችና መምህራን መካከል የተጠናከረ ግንኙነትን መፍጠር፣
- መምህራን ለትምህርቱ ሂደት ምቹ ሁኔታን እንዲፈጥሩ ማድረግና
- የተለያየ የመማር ስልት ያላቸውን ተማሪዎች መድረስ ናቸው፡፡

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ባህሪ ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው መምህራን አመቻች ሲሆኑ ተማሪዎች ደግሞ የራሳቸውን ትምህርት በራሳቸው እንዲማሩ ያደርጋል፡፡

ይህም ማለት ለትምህርት ይዘቱ የተቀመጡ ዓላማዎችን ከፍፃሜ ለማድረስ መምህራንና ተማሪዎች የጋራ ግባቸው መሆኑን ተረድተው በትብብር እንዲሰሩ ማድረግ ነው።

## 2.4. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ጠቀሜታ

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን ከመምህራን ጥገኝነት እንዲላቀቁ ያደርጋል። በመሆኑም ተማሪዎች ስለ ራሳቸው ትምህርት ራሳቸው እንዲወያዩ፣ እንዲመራመሩና ጥናታዊ ፅሑፎችን እንዲሰሩ የሚያበረታታ መድረክ ነው። በተጨማሪም ይህ አቀራረብ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ ለማድረግ ያስችላል (Reed and Bergemann (1995፣72-75)።

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን በተደራጀ የመማሪያ ክፍል ማስተማር ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ለማድረግ ያስችላል። ይህም በተማሪዎች መካከል የመተሳሰብና የመተባበር ባህል እንዲያድርባቸው እንዲሁም የተግባቦት ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል (Tsegaye 2001፣6)።

በተማሪዎችና መምህራን መካከል የሚታዩ ክፍተቶችን በማጥበብ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ከፍተኛ ትኩረት እንዲያደርጉ ያስችላል (Crokes and Chevdron 1991፣57)።

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ንቃት ባለው መንገድ የሚሳተፉበት ሲሆን የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎችም የሚከተሉት ናቸው።

- መማር ስኬታማ ሆኖ ከግብ እንዲደርስ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በማነሳሳት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥር ያደርጋል።
- መማር ሳቢ እንዲሆንና ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው በትምህርቱ ተሳታፊ በመሆን ተግባራትን መወጣት እንዲችሉ ይረዳል።
- ተማሪዎች የሚያገኙትን መረጃ ተጠቅመው ራሳቸውንና ህብረተሰቡን ወደ ተሻለ ህይወት እንዲለወጡ ያግዛል።
- ለተማሪዎች ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማሳየት እንዲመራመሩ፣ አካባቢያቸውን እንዲረዱ፣ ትንታኔ እንዲሰጡና እንዲያጠቃልሉ ያደርጋል Lue (1998፣3)።

በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ማስተማር ውጤታማ የሚሆነው ተማሪዎች ሲማሩ ብቻ ነው። ይህም ማለት መማር ትርጉም የሚያገኘው ተማሪዎች የተማሩትን በተግባር ማዋል ሲችሉ ነው፣ ትምህርትን አሳታፊና አይረሴ ማድረግ፣ ተማሪዎች እርስ

በዕርሳቸውና ከመምህራቸው ጋር መልካም ግንኙነትን እንዲፈጥሩ፣ በትምህርት ሂደት በመተጋገዝ፣ በመተግበርና ግልፅ የሆነ ውይይት በማድረግ ተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ እንደሚያመጡ ለማስቻል፣ ነገሮችን በጥልቀት ለመመርመር፣ ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመመልከት፣ ሀሳብ የማፍለቅና መቀበል እንዲሁም በውይይት የጋራ ስምምነት ላይ የመድረስ አቅምን ለማጎልበት በማስቻል በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው (ICDR 1999፣65-66)።

## 2.5. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ መርሆች

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የራሱ የሆነ መርሆች አሉት። ስለሆነም Temechegn (2002)ና ሙሉጌታ (1996) የሚከተሉን ዘርዝረዋል።

- ለተማሪዎች በራስ የመማር ሙሉ ሀላፊነትን መስጠት፡- ተማሪዎች ትምህርቱን ከማቀድ ጀምሮ እስከ መተግበር ድረስ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ በማድረግ የእርስ በእርስ የመማማር ሂደትን መፍጠርና ከመምህር ጥገኝነት ማላቀቅ

- የሚቀርበው ትምህርት በተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ የሚያመጣ መሆን፡- ይህም በተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ ያተኮረና የትምህርትን ዓላማ የሚያሳካ ሊሆን ይገባል ማለት ነው።

- ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሊሆን ይገባል፡- ተማሪዎች በግልና በቡድን በሚያደርጉት ተሳትፎ እርስ በእርሳቸው እንዲማማሩ ማድረግ ያስፈልጋል።

- በትምህርት ጊዜ መምህራን አመቻች መሆን፡- በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በራሳቸው እንዳይማሩ መሠናክል ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በማቃለልና በማስወገድ መምህራን ለትምህርቱ መሳካት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ መረጃዎችን መጠቆም፣ ገንቢ ምጋቤ ምላሽ መስጠትና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን አለባቸው።

- የተማሪዎችን የህይወት ልምድ ያገናዘበ ትምህርት ማቅረብ፡- ለተማሪዎች ከቤተሰባቸው እስከ ማህበረሰቡ ድረስ ያለውንና የሚያውቁትን የህይወት ልምድ ማዕከል ያደረገ ትምህርት ማቅረብ፡ ይህም አዲስ የሚያገኙትን እውቀት ከቀደመ

እውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ በጥልቅ እንዲመረምሩ መንገድ በማሳየት የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማስፋት ይረዳል።

- አበረታች ምጋቤ ምላሽ መስጠት፡- ተማሪው በክፍል ውስጥ በሚሳተፍበት፣ የክፍል ስራዎችን በሚያሳይበት፣ ጥያቄ በሚጠይቅበትና በሚመልስበት ወዘተ. ጊዜ ተማሪውን ለቀጣይ ስራዎች የሚያነቃቃና በውስጡ ያለውን እምቅ ሀይል አውጥቶ ለመጠቀም እንዲችል የሚያደርግ ነው።
- የተማሪዎችን የተለያየ ችሎታና የመማር ስልት ያገናዘበ ትምህርት ማቅረብ፡- ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ፍጥነት እንዲሁም በመስማት፣ በማየት፣ በመስራት ወዘተ. የመማር ስልት ያላቸው ናቸው።

## 2.6. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ መተግበሪያ መንገዶች

የተማሪ ተኮር ትምህርት መተግበሪያ መንገዶች የተለያዩና ብዙት ያላቸው ናቸው። ይህ ጥናት የሚዳስሳቸው ግን በአብዛኛው ተዘውትረው በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባር ላይ የሚውሉና የተማሪዎችን ትምህርታዊ ተሳትፎ የሚያበረታቱትን ሲሆን እንደሚከተለው ይገኛሉ።

### 2.6.1. በራስ/በግል የመማር ዘዴ

#### 2.6.1.1. በራስ /በግል/ የመማር ዘዴ ምንነት

በራስ የመማር ዘዴ ከስያሜው መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ትምህርቱን በግላቸው የሚማሩበት መንገድ ነው።

- በራስ የመማር ዘዴ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲማሩ እድል የሚያገኙበት ዘዴ ሲሆን በራስ የመተማመን፣ ጊዜን በአግባቡ መጠቀምና የትምህርት ሀላፊነትን ወስዶ መማርን የሚመለከት ጉዳይ ነው (ለማ 1998፣19)።
- በራስ የመማር ዘዴ ግለሰቦች በራሳቸው ተነሳሽነት በመማር ማስተማሩ ሂደት ሀላፊነት በመውሰድ የሚማሩበት ነው። ተግባር ላይ የሚውለውም ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ፍላጎት ለትምህርት ሲነሳሱ፣ ትምህርታዊ ዓላማ ሲኖራቸው፣ ከመምህራን ጋር በመተባበር ማስተማሪያ ዘዴዎችን መርጠው ሲጠቀሙና ትምህርታዊ ክንውኑን መገምገም ሲችሉ ነው (Knowles 1975፣8)።

- በራስ የመማር ዘዴ አንድን ተማሪ በትምህርት ሂደቱ በራሱ እንዲሰራ ማስቻል ሲሆን አቀራረቡም በቤት ስራ፣ በክፍል ስራ፣ በሙከራና በመሳሰሉት መልክ ሊከናወን ይችላል በማለት የዘዴውን የአተገባበር ስልት በድሩ (1990፣34) ገልፀዋል።

በአጠቃላይ በራስ የሚመራ ትምህርት ተማሪዎች ነፃነታቸውን በሚገባ ተረድተው ራሳቸውን ማስተዳደር፣ ትምህርታዊ ተግባራትን ማከናወንና ያለ ማንም ረዳትነት በግል መማር መቻል ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ መምህራንም ሁሉንም ነገር ለተማሪዎች ብቻ የሚተውበት ሳይሆን ለትምህርቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ በማመቻቸትና አቅጣጫ በማስያዝ የተማሪዎች በራስ የመማር ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ክትትል የሚያደርጉበት ስልት መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

### 2.6.1.2. በራስ የመማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

Candy (1991፣51-58) በራስ የመማር ዘዴን ጠንካራ ጎኖች እንደሚከተለው ገልፀዋል።

- ተማሪዎች ስለራሳቸው የመማር ሂደት ሃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግ፣
- የተማሪዎችን ግላዊ የፈጠራ ሂደት ማሳደግ፣
- የተማሪዎችን ተነሳስኦትና ችሎታ በከፍተኛ ደረጃ ማጎልበትና
- ለትምህርቱ ግልፅነት አስተዋፅኦ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል።

መለስ (1988፣20) በራስ የመማር ዘዴን ጠንካራ ገጽታዎች በሚከተለው ሁኔታ ዘርዝረዋል።

- እያንዳንዱ ተማሪ የሚገኝበትን የትምህርት፣ ፍላጎትና የእውቀት ደረጃ ለመገምገም ይረዳል።
- መረጃ የመሰብሰብ፣ ማጠናከር፣ መተንተንና በሪፖርት መልክ ማቅረብን ያለማምዳል።
- እያንዳንዱ ተማሪ በራሱ ፍጥነት እንዲማር ያደርጋል።
- የመጠየቅ፣ መመራመር፣ መረጃዎችን የመመዝገብና የማቅረብ ክህሎትን ያዳብራል።
- አርቆ ማሰብን፣ ፈጠራንና በራስ የመተማመን ሀይልን ያጎለብታል የሚሉት ይገኙበታል።

ይሁን እንጂ በራስ የመማር ዘዴ ተማሪው ሀላፊነት እንዲሰማውና ትምህርቱን በአግባቡ እንዲከታተል በማድረግ መልካም ገጽታ ያለው ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ድክመት እንደሚታይበት ምሁራን ገልፀዋል።

መለሰ (1988፣20) ሲገልጹ የሚሰጠው የግል ስራ ከተማሪዎች አቅም በላይ ከሆነ ተስፋ በማስቆረጥ የበታችነት ስሜትን ይፈጥራል ብለዋል። በተመሳሳይ ለማ (1998፣19) በግል የመማር ዘዴን ከመጠን ያለፈ አዘውትሮ መጠቀም ደግሞ በተማሪዎች ዘንድ የግለኝነት ስሜት እንዲፈጠር ያበረታታል በማለት ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በግል የመማር ዘዴ የተማሪውን በራስ የመስራት ልምድ የሚያጎለብት መሆኑና እያንዳንዱን ተማሪ ለመገምገም ማስቻሉ አወንታዊ ገጽታው ሲሆን በሚገባ ካልተተገበረ አሉታዊ ገጽታዎችም እንዳሉ ተረድተናል። ይሁን እንጅ መለሰ (1988፡20) በግል የመማር ዘዴን ውጤታማነት ለማሳደግ የግል ስራዎች የተማሪዎችን ችሎታ ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፤ በተወሰነ ዓላማ ላይ የተመሰረቱ ስራዎችን በመስጠት፣ ግልፅና የማያሻሙ መመሪያዎችን ማስቀመጥና የተማሪዎችን የእርስበእርስ ትብብርን የሚያበረታቱ እንዲሆኑ በማድረግ መምህራን የራሳቸውን አስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ነው ብለዋል።

## 2.6.2. በቡድን የማስተማር ዘዴ

### 2.6.2.1. በቡድን የማስተማር ዘዴ ምንነት

ማሪው (1987፣91) የቡድን ማስተማር ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት ጉልህ ድርሻ እንዳለው የታወቀው ከ1930 ወዲህ ነው ብለዋል። የቡድን ማስተማር ዘዴ ተማሪዎችን በቡድን መድቦ በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ እንዲወያዩና እንዲመራመሩ እንዲሁም ከውይይቱ መጨረሻም ግልፅ ያልሆኑላቸውን ጉዳይ እንዲጠይቁ የሚደረግበት የማስተማር ዘዴ ነው (አብዱራሁማን 1983፣46)።

የቡድን ስራ በርካት ያሉ ሰዎች በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ በቃል ሀሳብ እየተለዋወጡ የሚማሩበት መንገድ ነው። በዚህ ጊዜም ለአንድ ጥያቄ የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ክርክር የሚደረግበት መድረክ መሆኑን ያስገነዝባል በማለት መለሰ (1988፣18) ገልፀዋል።

በአጠቃላይ የቡድን ማስተማር ዘዴ ማለት የተወሰኑ ተማሪዎች ሰብሰብ ብለው የሚወያዩበት፣ የሚከራከሩበት፣ የሚመራመሩበትና በመጨረሻም ወደ አንድ ውሳኔ የሚደርሱበት ዘዴ ነው።

### 2.6.2.2. የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠቀሜታ

የቡድን ስራ እንደስራው ዓይነትና ባህሪይ፣ እንደ መምህሩና ተማሪዎች ልምድ የተለያየ ቢሆንም የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደግና ስለ ትምህርታቸው ሀላፊነት ወስደው ራሳቸውን እንዲያስተምሩ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ስለሆነም ምሁራን ስለቡድን ስራ ጠቀሜታ የሚከተለውን ብለዋል።

- የቡድን ማስተማር ዘዴ በክፍል ውስጥ ማራኪ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ከማስቻሉ ባሻገር የተማሪዎች ትምህርታዊ ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋል (Long and Porter 1985)።
- የቡድን ማስተማር ዘዴ አንድን ሀሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው (በድሩ 1990፣37)።

Light & Roycox (2001፣117)ና Melese (1999፣13) የቡድን ማስተማር ጠቀሜታ ናቸው ያሏቸውን ከዚህ በታች እንደሚታዩት ዘርዝረዋል።

- በግል ለመስራት የሚያስቸግሩ ተግባራትን በትብብር ለመስራት ያስችላል።
- በመምህራንና ተማሪዎች መካከል ጤናማ መስተጋብር እንዲኖር ያደርጋል።
- በተማሪዎች ዘንድ የእርስ በእርስ መማማር ባህልን ያዳብራል።
- የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ያዳብራል።
- የመደማመጥና መቻቻል ስርዓትን ያለማምዳል።
- አይን አፋር ተማሪዎችን ከሰው ፊት መናገር እንዲችሉ ያበረታታል።
- ተማሪዎችን በትምህርት ሂደቱ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ያደርጋል።

### 2.6.2.3. የቡድን ማደራጃ መንገዶች

በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የቡድን ስራ ማስተማር ዘዴ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ተማሪዎችን በቡድን መመደብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ቡድን ለማደራጀት ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ካለባቸው ጉዳዮች መካከል ምሁራን የሚከተሉትን ነጥቦች ዘርዝረዋል።

ችሎታ፡- አንድ ቡድን በተመሳሳይ ወይም በቅይጥ ችሎታ ሊደራጅ ይችላል። ይሁን እንጅ የተለያየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች አቀላቅሎ በአንድ ቡድን መመደብ በተለይም ለደካማ ተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ምክንያቱም ደካማው ከጠንካራው ተማሪ ግልጽ ያልሆነለትን ነገር ሲማር ጠንካራውም ባስተማረ ቁጥር ለራሱም የበለጠ እየተረዳው ይሄዳል (Harmer 1991)ና Frrant (1980)።

ፆታ፡- እንደ ችሎታ ሁሉ በቡድን ምደባ ጊዜ የፆታ ጉዳይም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ምክንያቱም ወንድና ሴት ተማሪዎች እህታዊና ወንድማዊ ስሜት አድሮባቸው በትምህርታዊ ጉዳዮች መወያየትና መረዳዳት እንዲችሉ ማድረግ ነው። ይሁን እንጂ በቡድን አደረጃጀት ጊዜ ከፆታ ይልቅ ለችሎታ ቅየጣ የበለጠ ትኩረት ቢሰጥ የቡድን ማስተማርን ዓላማ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል Farrant (1980)።

የቡድን አባላትን ቁጥር መወሰን፡- በቡድን ምደባ ጊዜ ሌላውና ከግምት መግባት ያለበት ጉዳይ የቡድን አባላትን ቁጥር መወሰን ነው። የአንድ ቡድን አባላት ቁጥር የሚወሰነው እንደስራው ዓይነትና ባህሪይ ነው። ይሁን እንጅ በአንድ ቡድን ውስጥ የአባላትን ቁጥር Doff (1988) ከአራት እስከ አምስት፣ Mc Greal (1988:18) ከአራት እስከ አምስት፣ ለማ (1998) ከሶስት እስከ ስድስት፣ መለሰ (1988፣18) ከአራት እስከ አምስት፣ Byrne (1992) አራት እስከ ስምንት ሊሆን ይችላል በማለት ገልፀዋል። በተጨማሪም ማረው (1987)ና ደረጀ (1999) በአንድ ቡድን ውስጥ የአባላት ቁጥር አነስተኛ ቢሆን ይመረጣል። ምክንያቱም በውይይት ጊዜ የሀሳብ ልዩነትን አበላልጦ ወደ አንድ ውሳኔ ለማድረስ እንዲቻል፣ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግና ተሳትፏቸውን ለመቆጣጠር አመቺነት አለው ብለዋል።

ጠቅለል አድርገን ስናየው የአንድ ቡድን አባላትን ቁጥር ለመወሰን ከስራው አይነትና ባህሪይ እንዲሁም ከተማሪዎችና መምህራን ልምድ የሚነሳ ነው። ይሁን እንጂ ለስራው ውጤታማነት ግን የአባላት ቁጥር አነስተኛ ቢሆን ይመረጣል ስለሆነም የቡድን አባላትን ቁጥር ቁርጥ አድርጎ ይህንን ያህል ነው ማለት እንደማይቻል ተረድተናል።

የቡድን መሪ፡- የቡድን መሪ አስፈላጊነት እንደ ስራው አይነትና ባህሪይ የሚወሰን ቢሆንም መኖሩ ግን ቢያንስ ለሚከተሉት ነገሮች ይጠቅማል።

- የቡድን መሪው የቡድኑ ስራ በሁሉም አባላት ተሳትፎ መሰራቱን ይቆጣጠራል።

- የቡድን አባላት እርስ በእርስ ሲተራረሙ፣ ሲከራከሩና በጋራ ሲሰሩ በመጠኑም ቢሆን የመምህሩን ተግባር ተክቶ የማስተባበር ስራን ይፈጽማል(ማረው 1987)፡፡

በተጨማሪም ማረው በቡድን ስራ ጊዜ የቡድን መሪ መኖሩ በቡድኑና በመምህሩ መካከል ጠንካራ ግንኙነትን በመፍጠር ተማሪዎች በነፃነት መሳተፍ እንዲችሉ ያበረታታል፡፡ ስለሆነም መምህራን የቡድን መሪን አስፈላጊነት ከስራው አይነትና ባህሪይ አንጻር አገናዝበው ማስመረጥ ይጠበቅባቸዋል በማለት ገልጸዋል፡፡

### 2.6.2.4. የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

የቡድን ማስተማር ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት የራሱ የሆኑ አወንታዊ ገጽታዎች አሉት፡፡

ማረው (1987፤38)፣ ደባሱ (1990፤26)ና መለሰ (1988፤19) የቡድን ስራን አወንታዊ ገጽታዎች በሚከተለው ሁኔታ አስፍረዋል፡፡

- ተማሪዎችን በቋንቋው በስፋት እንዲለማመዱ በር ይከፍታል፡፡
- በተማሪዎች እርስ በእርሳቸውም እንዲረዳዱ ነፃነት ይሰጣል፡፡
- ተማሪዎችን በራሳቸው እንዲተማመኑ ያደርጋል፡፡
- አንድን ሃሳብ ከተለያየ አቅጣጫ ለማየት ያስችላል፡፡
- በተማሪዎች መካከል ጠንካራና ዘላቂነት ያለው ግንኙነትን ለመፍጠር ያስችላል የሚሉት ናቸው፡፡

የቡድን ማስተማር ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት አዎንታዊ ገጽታዎች እንዳሉት ሁሉ አሉታዊ (ደካማ) ጎኖችም አሉት በማለት Doff (1988፤40) የሚከተሉትን ነጥቦች ገልጸዋል፡፡

- በቡድን ስራ ጊዜም ድምጽ ይበዛል ድምጹም ከጎረቤት ያሉ ሰዎችን ሊረብሽ ይችላል፡፡
- ተማሪዎች ስህተት እንዲሰሩ ይጋብዛል፡፡
- የእያንዳንዱን ተማሪ ስራ ለመቆጣጠር ያዳግታል፡፡
- በውይይት ጊዜ በአባላት መካከል አለመግባባትና ወደ አንድ ድምዳሜ ለመድረስ ያስቸግራል፡፡
- በውይይት ወቅት ተሳትፎ የማያደርጉ ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

- የቡድን ስራው ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል የሚሉት በአሉታዊ ገጽታ የሚታዩ ናቸው።

### 2.6.3. ችግር ፈች የማስተማር ዘዴ

#### 2.6.3.1. የችግር ፈች ማስተማር ዘዴ ምንነት

ችግር ማለት ባለውና በሚፈለገው ነገር መካከል የሚታይ ክፍተት ሲሆን ችግር ፈች ዘዴ ደግሞ ክፍተቱን ለመሙላት ወይም ችግሩን ለማስወገድ የሚያስችል የመፍትሔ ሃሳብን ማፈላለጊያ መንገድ ነው (Opwis፣1994)። በተመሳሳይ Nachmias and Nachmias (1987) የችግር ፈች ማስተማር ዘዴ ለመማር አነቃቂ የሆነና ለአንድ ችግር ሳይንሳዊ የሆነ መፍትሄ የሚፈለግበት ነው ብለዋል።

ችግር ፈች የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርቱን ከነባራዊና ከሚታወቅ ችግር እንዲነሳ በማድረግ የተማሪዎችን የችግር አፈታት እውቀት እንዲጨብጡና ችግር ሲገጥማቸው በራሳቸው የመፍታትን ልምድ እንዲያዳብሩ የሚደረግበት ስልት ነው (ሙሉጌታ 1996)።

ችግር ፈች የማስተማር ዘዴ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ለችግሮች መፍትሔ መፈለግን የሚከተል ዘዴ ነው። ዘዴውም በግል ወይም በቡድን ሊከናወን የሚችል ነው (መለስ 1988፣22-23)።

በአጠቃላይ የችግር ፈች ዘዴ ማለት ለተማሪዎች ችግር ከተከሰተ በኋላ መፍትሄ ማፈላለግን ብቻ የሚያስተምር ሳይሆን አንድ ነገር ለመስራት በሚታቀድበት ጊዜም ሊገጥም የሚችልን ችግር ከወዲሁ በማሰብ መወሰድ ያለበትን እርምጃ ማስገንዘብንና አስቀድሞ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት የሚረዳ ስነ-ዘዴ ነው።

#### 2.6.3.2. የችግር ፈች ማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

የችግር ፈች ማስተማር ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት አወንታዊ ገጽታዎች እንዳሉት መለስ (1988፣23) የሚከተለውን ብለዋል።

- ጥልቅ እውቀትን ለመጨበጥና ጠቃሚ ክህሎትን ለማዳበር ይረዳል።
- በህይወት ጎዳና ያሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቋቋም ያዘጋጃል።
- ያለፈውን ጊዜ በማሰብ ለወደፊት አርቆ ማየትና የመመርመር አቅምን ያጎለብታል።

- ከተለያዩ ከስተቶች ለመማርና የአስተሳሰብ አድማስን ለማስፋት ያግዛል፡፡
- የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማዳበር ይረዳል፡፡

በተጨማሪም መለስ የችግር ፈች ዘዴ ደካማ ጎኖች ናቸው ያሏቸውን ከዚህ ቀጥሎ ገልጸዋል፡፡

- ለተማሪዎች በቂና መደበኛ የሆነ ማስታወሻ አለማስያዙ፣
- ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ይዘት ሲገጥማቸው ተስፋ እንዲቆርጡ ማድረጉ፣
- ስፊ የትምህርት ይዘትን በአጭር ጊዜ ለማስጨበጥ መሞከሩና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 2.6.4. የሚና ጨዋታ ዘዴ

### 2.6.4.1. የሚና ጨዋታ ዘዴ ምንነት

የሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴ ከሁሉም የትምህርት አይነቶች በተለየ ሁኔታ በቋንቋ ትምህርት ሰፊ አገልግሎት እንደሚሰጥ ይታመናል፡፡ ይህ ዘዴ እንደ ድራማ ሰፊ ቅድመ ዝግጅት የማይፈልግና የተለያየ ገፀ-ባህሪን በመላበስ በህይወት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ትምህርታዊ ጉዳዮችን በትዕይንት መልክ ለማቅረብ የሚያስችል ዘዴ ነው (Amenu 2005)::

በሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች በተውኔት መልክ የተወሰነ የስራ ድርሻ ሲሰጣቸው ልክ በእውነተኛ ስራ ላይ እንዳሉ አስመስለው ውሳኔ በመስጠት፣ ባለጉዳይን በመቀበል ስራን ማከናወን እንዲችሉ በቂ ስልጠና የመስጠት ስራ ነው (ደባሱ 1990፡37)፡፡

ከምሁራኑ ገለፃ እንደምንረዳው የሚና ጨዋታ ዘዴ ማለት ማስተማር የተፈለገውን ትምህርት በድራማና ተውኔት መልክ በማቅረብ ተማሪዎችን እያዝናኑ ቁም ነገር የማስጨበጥ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ በጉዳዩ ተሳታፊ ስለሚያደርግ ተረድኦትን በማዳበር ትምህርቱን አይረሴነት እንዲኖረው የሚያደርግ ማስተማሪያ ዘዴ ነው ማለት እንችላለን፡፡

#### 2.6.4.2. በሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

የሚና ጨዋታ ማስተማር ዘዴን ጠንካራ ጎኖችን መለሰ (1988፣26)፣ ደባሱ (1990፣37)ና Amanu (2005:29) እንደሚከተለው ገልፀዋል።

- የተማሪዎችን የመማር ተነሳስኦት፣ ስሜትና አመለካከት ለማሳደግ ያስችላል።
- ስለ ማህበራዊ ህይወትና የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች ጥልቅና ግልጽ የሆነ ተረድኦትን ይፈጥራል። ይህም ተማሪዎችን ለእውኑ አለም ያዘጋጃል፣ አስተዳደራዊ ስራንም ያለማምዳል።
- የፈጠራ ችሎታና በራስ መተማመንን ያጎለብታል።
- ከህይወት ገጠመኞች ጋር ለመለማመድ ይረዳል።
- ግልፅ የማስተማሪያ ዘዴ በመሆኑ ተጨባጭ የትምህርት አካባቢን የሚፈጥርና ሰፊዝግጅትን የማይጠይቅ ነው።
- የተማሪዎችን የምልከታ፣ የማገናዘብ፣ የፈጠራ፣ የመተንተን፣ የመጻፍና ውሳኔ የመስጠት ክሂሎትን ለማዳበር ይረዳል።
- በትግበራ ጊዜም ታዳሚዎች ከማየትና ከመስማት አልፎ የተግባሩ ተካፋዮች እንዲሆኑ ያደርጋል።

ሆኖም ይህ የማስተማር ዘዴ በሚገባ ካልተተገበረ የሚከተሉት ደካማ ጎኖች ይታዩበታል።

የሚቀርበውን ትወና እንደ መዝናኛ በማየት ቁም ነገሩን የመዘንጋት፣ ሰፊ ሰዓትን የመውሰድ፣ ማስተላለፍ ከተፈለገው መልዕክት ያለፈና የተጋነነ ነገር የማቅረብ፣ በተማሪዎች ዘንድ ተዋንያንን ከትወና በኋላ ተላብሰው በሰሩት ገፀ ባህሪይ ወክሎ መጥራትና የማሸማቀቅ ሁኔታ ሊኖር ይችላል (መለሰ 1988፣26)፣ ለማ (1998፣13)፣ ደባሱ (1990፣37)፣ ICDR (1999፣86)።

### 2.6.5. በፕሮጀክት ሥራ የማስተማር ዘዴ

#### 2.6.5.1. በፕሮጀክት ሥራ የማስተማር ዘዴ ምንነት

የፕሮጀክት ሥራ በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ አንዱና ተቀባይነትን እያገኘ ያለው የማስተማሪያ ዘዴ ነው። በዚህ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች ምን መስራት እንደሚገባቸው በራሳቸው ይወስናሉ። ተግባራትን ይመርጣሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይሠራሉ ከዚያም ለክፍሉ ሪፖርት ያቀርባሉ። በዚህ ዘዴ የመምህሩ ሚና የተማሪዎችን ሥራ

በመከታተልና በማረጋገጥ እንዲሁም እገዛ በማድረግ ላይ የተወሰነ ነው (Mulkalel 1998:77)።

የፕሮጀክት ሥራ በግል ወይም አነስተኛ በሆነ ቡድን ሊተገበር የሚችል ነው። ይህም የሚነደፈው ተማሪዎች አዳዲስ ፅንሰ ሀሳቦችን እንዲተዋወቁና ያልተለመዱ ተግባራትንና መሳሪያዎችን ካለፈ እውቀታቸው ጋር በማቀናጀት መስራት እንዲችሉ ለማድረግ ነው Walkin (1989፣235)።

እንዲሁም Aggrawal (1996፣241) የፕሮጀክት ስራ ማለት ዓላማ ያለው ከገሀዱ ዓለም ተግባራት የሚመሰረት ወይም የገሀዱን ዓለም የሚወክል፣ ችግርን ማዕከል ያደረገ፣ ለተማሪዎች በራሳቸው የመማር ሀላፊነትና ነፃነት የሚሰጥ ነው ብለዋል።

### 2.6.5.2. የፕሮጀክት ሥራ የማስተማር ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

የፕሮጀክት ስራም ልክ እንደሌሎች የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ሁሉ የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት።

ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል በዋናነት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- ተማሪዎች ለትምህርታቸው ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል።
- አራቱን የቋንቋ ክሂሎች አቀናጅተው እንዲጠቀሙ ያበረታታል።
- የተማሪዎችን የእርስ በእርስ መስተጋብር ያጠናክራል።
- ተማሪዎች ከአካባቢያቸው እንዲማሩ እድል ይፈጥራል።
- ተማሪዎች እቅድ መንደፍ፣ ማደራጀት፣ መምራት፣ መቆጣጠርና ሪፖርት ማቅረብ እንዲችሉ ያግዛል።
- የክፍል ውስጥ ትምህርትን በተግባር ለመተርጎም ያስችላል (ለማ 1998፣17)፣ ደባሱ (1990፣41))።

Smith (2004) የፕሮጀክት ሥራ ማስተማሪያ ዘዴም በሚገባ ካልተተገበረ የሚከተሉት ድክመቶች እንደሚታይበት ገልፀዋል።

- የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።
- በፕሮጀክቱ ሥራ ሁሉም ተማሪ እኩል ላይሰራ ይችላል።
- መረጃ ለመሰብሰብና ሪፖርት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ይወስዳል።
- የቡድን ሥራ በመሆኑ የግለሰብን ለውጥ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።

በአጠቃላይ የተማሪ ተኮር ትምህርት መተግበሪያ መንገዶች ተማሪዎችን በስፋት የሚያሳትፉ ናቸው። በግል የተለያዩ ተግባራትን መስራት፣ በቡድን መወያየት፣ ትንታኔ መስጠትን፣ ችግር መፍታትን፣ ከተግባር ጋር የተቀናጀ ትምህርት ማካሄድን በተማሪዎች ዘንድ ለማስረጽ ይረዳሉ። ስለሆነም በእለት ከእለት የመማር ማስተማር ሂደት አንድ አይነት ዘዴን ከመጠቀም ይልቅ እንደ ትምህርቱ ይዘትና ባህሪይ እንዲሁም እንደ አካባቢው ሁኔታ የተለያዩ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም የተለያዩ ማስተማሪያ ዘዴዎች ተግባራዊ በተደረጉ ቁጥር የተማሪዎችን የመማር ልዩነት ለመድረስ ይቻላል።

## 2.7. በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የመምህሩና የተማሪው ሚና

### 2.7.1. የመምህሩ ሚና

በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና የትምህርቱን ሂደት ማመቻቸት፣ መረጃዎችን መጠቀምና ተማሪዎች ለሚጠይቁት ነገር ሁሉ አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግ ሀላፊነት ነው።

በዚህ አቀራረብ የመምህሩን ሚና ICDR (1999፤72)፤ Rogers (2002፤19)፤ Yalew (2004፤21) ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል።

- ተማሪዎችን ለትምህርት ማነቃቃት፤
- የትምህርቱን ዓላማ ማስተዋወቅ፤
- ለትምህርቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መጠቀም፤
- የተለያዩ ተግባራትን የአሰራር ስልት መጠቆም (አቅጣጫ ማመላከት)፤
- የተሰሩ ስራዎችን በመከታተል ማረምና ገንቢ ምጋቤ ምላሽ መስጠት፤ የተማሪዎችን የተለያየ የመማር ስልት መለየት፤
- የተማሪዎችን የመማር ለውጥ ማጥናት፤
- ከተለያዩ ተማሪዎች የሚሰነዘሩ ጥያቄዎችን፣ መልሶችንና አስተያየቶችን እኩል በሆነ መልኩ ማስተናገድ፤
- በመማር ማስተማሩ ሂደት ማራኪ ድባብ እንዲፈጠር ማድረግ፤

- በክፍል ውስጥ የግልና የቡድን ስራዎችን በመስጠት ተዘዋውሮ ምልከታ ማካሄድና ችግር ሲኖር ማስተካከያ መስጠት፣
- በተቻለ መጠን በቡድን ውይይት ጊዜ እንደ አንድ የቡድን አባል በመሆን መሳተፍ የሚሉትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ጊዜ የመምህሩ ሚና የተለያ ትምህርታዊ ይዘቶችን ከማቀድ ጀምሮ እስከ ምዘና ድረስ ያለውን ተግባር ያካናውናል፡፡ የመማር መስተማሩን ሂደትም ውብና ማራኪ በማድረግ በተማሪዎች ዘንድ የመማር ተነሳስኦትን የሚፈጥር ነው፡፡ ስለሆነም መምህር ትምህርትን ፍትሀዊ አድርጎ የታቀደውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል የጠለቀ ሙያዊ እውቀትና ተፈጥሯዊ ብስለት ሊኖረው ይገባል በማለት Tudor (1996) ገልጸዋል፡፡

### 2.7.2. የተማሪው ሚና

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የትኩረት አቅጣጫውን በተማሪዎች ላይ በማድረግ አብዛኛውን የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በራሳቸው ተግባርና ተሳትፎ እንዲሸፍኑት ማድረግ ነው፡፡ ይህም በተማሪዎች ዘንድ ዘላቂ የሆነ የባህሪይ ለውጥን ለማስገኘት ይረዳል፡፡

በመሆኑም በዚህ አቀራረብ የተማሪዎች ተግባር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- በትምህርት ሰዓት ፍዝ ተመልካች ከመሆን ይልቅ በንቃት መሳተፍ፣
- በትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ሀላፊነትን በመቀበል የእኔነት ስሜት መፍጠር፣
- የራስን የመማር ልምድ መለየት፣
- በትምህርታዊ ጎዳዮች ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ምክንያታዊ መሆን፣
- የግልና የቡድን ስራዎችን መስራትና መምራት መቻል፣
- በቡድን ውይይት ጊዜ መደማመጥና መረዳዳት መቻል፣
- የተሰሩ ስራዎችን በቃልም ሆነ በጽሑፍ ክፍል ውስጥ ማቅረብ፣
- ግልፅ ያልሆኑ ፅንሰ ሀሳቦችን መጠየቅና ለሚጠየቁ ጥያቄዎችም መልስ መስጠት፣
- ከመምህራን ጋር በመተባበር የትምህርት ይዘቶችንና የምዘና ስልቶችን መምረጥና መወሰን ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው Nunan (1988፣ 81-52) Tilaka (1998፣9-10)፣ Amanu (2005፣28)፡፡

በአጠቃላይ ከድርሳናት እንደምንረዳው በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ጊዜ ተማሪዎች የትምህርት ይዘቱን መምረጥ፣ ማቀድ፣ ማዘጋጀት፣ መወሰን፣ መተግበርና የምዘና ሂደቶችን ውሳኔም ሳይቀር ከመምህራን ጋር በመተባበር ያከናውናሉ። በተጨማሪም በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችና መምህራን የየስራ ድርሻቸውን ተረድተው የተጣለባቸውን ሀላፊነት የሚወጡበትና ሁለቱም አካሎች የታቀደውን ዓላማ በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቅ የሚተጉበት ነው ማለት እንችላለን።

## 2.8. በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

በመስኩ ያሉ ምሁራን በተማሪ ተኮር ትምህር ትግበራ ጊዜ እንቅፋት ከሚፈጥሩ ነገሮች መካከል የሚከተሉትን ገልፀዋል።

### 2.8.1. የለውጡ ባህሪይ

የተማሪ ተኮር ትምህር ትግበራ በሀገራችን ከ1994ዓ.ም ጀምሮ የሚተገበርና ከተለመደዉ ማስተማሪያ ዘዴ የተለየ ለዉጥ እያሳየ ያለ ነዉ። በመሆኑም ይህ ለውጥ በስራ ሲተረጎም ከአካባቢ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ ከሄደ ውጤታማ ይሆናል። አዲስ ለውጥ ግቡን የሚመታ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ነው።

- አዲሱ ለውጥ ግልጽ የሆነ ዓላማ ሲኖረው፣
- የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ በመገንዘብ የመማር ፍላጎት መፍጠር ሲችል፣
- ለመተግበር በቂ የሆኑ የትምህርት መሳሪያዎች ሲኖሩት፣
- ተግባሪው አካል በሚገባ ስልጠና ወስዶ የለውጡን ባህሪያት ሲረዳ ነው። ከዚህ ውጭ ሲሆን ግን በትግበራው ላይ ተፅዕኖ ይፈጠራል (Farrant 1980፣97)።

### 2.8.2. የመምህራን አመለካከት

መምህራን ከለውጡ ጋር ግጭት የሚፈጥሩበት ሁኔታ አለ። ይህም ግጭት ከአዳዲስ መማሪያ መጽሐፍት ጋር አለመጣጣም፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለውጥ አለመረዳት፣ ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር አለማመቻቸት ወዘተ. ናቸው (Tudor 1996፣230)። በተጨማሪም McCombs and Whisler (1997፣200) በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ መምህራን የለውጡ ቁልፍ ሚና ተጫዋቾች በመሆናቸው የእነርሱ ለለውጥ አለመዘጋጀት ትግበራውን ያደናቅፈዋል በማለት ገልጸዋል።

### 2.8.3. ለመምህራን የሥራ ላይ ስልጠና አለመስጠት

መምህራን የሰለጠኑበት አቅጣጫና የተማሪ ተኮር ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራ አንድነት ከሌለው በትግበራውና መምህራን መካከል አለመግባባት ይፈጠርና ትግበራው ሊደናቀፍ ይችላል (Tudor 1996፣234)። Tudor ለመምህራን የስራ ላይ ስልጠና መምህራን የሰለጠኑበት መንገድ ከአዲስ ትግበራ ጋር እንዲስማማ ማድረግ መሆኑን አብራርተዋል።

### 2.8.4.ለተማሪዎች ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና አለመስጠት

በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ እንቅፋት ሊፈጠርባቸው ከሚችላቸው መንገዶች አንዱ ለተማሪዎች ስለ አዲሱ አቀራረብ ስልጠና ካለመስጠት የተነሳ የሚከሰት ነው። Tudor (1996፣41) የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ በመምህራንና በተማሪዎች አማካኝነት የሚከናወን ነው በማለት እስለዉም መምህራን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው ስልጠና ሊወስዱ እንደሚገባ ሁሉ ለተማሪዎችም በዚህ አቀራረብ እንዴት መማር እንዳለባቸው ስለ አቀራረቡ ምንነት፣ ዓላማና ጠቀሜታ ወዘተ. ቅድመ ሁኔታዎችን ማሳወቅ አቀራረቡን ስኬታማ ያደርገዋል ብለዋል።

### 2.8.5. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ መሳሪያዎች አመች አለመሆን

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ሊገደብ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አመች አለመሆን ነው።

በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች እንደልባቸው እየተሽከረከሩ የሚቀመጡበትና በቡድንም ሆነ በጥንድ የስራ ተግባር ወቅት እንደፈለጉ ለመንቀሳቀስ የሚያስችሉ ወንበሮች ሊኖሩ ይገባል። በተጨማሪም የመማሪያ መጻሕፍት ከተማሪዎች ቁጥር ጋር አለመመጣጠን፣ ስዕሉች፣ ቻርቶች፣ ፖርስተሮች ወዘተ. አለመኖር በትግበራው ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ (Farrant 1980፣50)።

### 2.8.6. የመማሪያ ክፍሉችና የተማሪዎች ቁጥር አለመመጣጠን

በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ብዙ ተማሪዎች የሚማሩ ከሆነ በቡድን የተለያዩ ተግባራትን ለመስራት፣ መምህሩ ለእያንዳንዱ ቡድን (ተማሪ) በቂ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠትና ሁሉም ተማሪ እንዲሳተፍ እድል ለመስጠት አስቸጋሪ ይሆናል።

Leu (1998፣17) መምህራን በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ ተማሪዎችን አጣበው የሚያስተምሩ ከሆን ከተፈለገው ዓላማ ለመድረስ ችግር ሊፈጥርባቸው ይችላል። ምክንያቱም የቡድን፣ ፕሮጀክት፣ ሚናጨዋታና ችግር ፈች የማስተማር ዘዴዎችን ለማከናወን ይቸገራሉ ብለዋል።

ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ በመጋራትም Shank (1999፣10) አነስተኛ የተማሪዎች ቁጥር ባለበት ክፍል ውስጥ ማስተማር የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን ለመተግበር፣ ተማሪዎችን በትምህርት ሂደቱ ለማሳተፍና የእያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ ለመገምገም ያስችላል በማለት አጽንኦት ሰጥተው ገልጸውታል።

### 2.8.7. አካባቢና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች

የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራን ሊያደናቅፍ ከሚችሉ ምክንያቶች ውስጥ አካባቢና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው።

Moore (2001፣53) ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ አመች ቦታ፣ ጊዜ የአየር ሁኔታ ሊኖር ይገባል በማለት ገልጸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታም Fisseha (2001፣53) አንድ የመማሪያ ክፍል በቂ ብርሃንና ንፁህ አየር ከሌለው፣ ጫጫታ የሚበዛበትና የመጠጥም ይሁን የሌላ "ግሮሰሪ" ከአካባቢው ያለበት ከሆነ ትምህርት ትግበራው ላይ አሉታዊ ገጽታ እንደሚያስከትል ገልጸዋል።

### 2.8.8. በቂ ጊዜ አለመኖር

የማስተማሪያ ጊዜና የመጽሐፍት ይዘት አለመመጣጠን የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራን ይገድባል። Shank (1999፣53) የማስተማሪያ ሰዓት እጥረት ሲገጥም የሚፈለገውን የማስተማሪያ ዘዴ መርጦ ለማስተማር አዳጋች ይሆናል። ሰፊ የሆነ የማስተማሪያ ጊዜ ሲኖር የተማሪ ተኮር ትምህርት በተገቢው መንገድ ሊተገበር ይችላል። የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን ለመተግበርም ያስችላል። የጊዜ እጥረት ካለ ግን መምህሩ ቀጥተኛና መምህር መራሹን ዘዴ እንዲጠቀም ይገደዳል በማለት ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ ተዕዕኖ የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ሰው ሰራሽና ሰውሰራሽ ያልሆኑ ነገሮች ብለን ልንከፍላቸው እንችላለን ማለት ነው።

## 2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር የምንመለከተው ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸውን ቀደምት ስራዎች ነው።

ሙሉጌታ ይታየው (1996) "የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በኮሙተኮ ሰርትፊኬት መርሃ ግብር" በሚል ርዕስ አጥንተዋል። የጥናቱ ዓላማም በተጠቀሰው ኮሌጅ የሰርትፊኬት መርሃ ግብር አቀራረብ ያለውን የአተገባበር ሁኔታ መፈተሽ ነው። አጥኚው የጥናቱን ተተኳሪዎች ለመምረጥ የታቀደ ናሙና ዘዴን የተጠቀሙ ሲሆን መረጃዎችን ለመሰብሰብ ደግሞ ያልተደራጀ ምልከታ /unstructured observation/፣ የቪዲዮ ቀረጻ፣ የተማሪዎችን የእለት ሁኔታ ማስታወሻን፣ የጽሑና የቃለ መጠይቅን በአጋዥነት ተጠቅመዋል። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘውን ውጤትም በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተንትነዋል። የጥናቱ ውጤትም በኮሌጁ በተጠናው መርሃግብር የተማሪ ተኮር ትምህርት ሲተገበር የታየ ቢሆንም በቡድኖች አደረጃጀት የአባላት ቁጥር መብዛት፣ ሁሉም የቡድን አባላት በጋራ ስራዎች ላይ እኩል ተሳትፎ አለማድረግና የጊዜ እጥረት የሚሉት ችግሮች አቀራረቡን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገጥሙ ችግሮች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኢልያስ አድማሱ (1997) "በኦሮሚያ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ መሠረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ" ነው። የጥናቱ ዓላማ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ መምህራን ኮሌጆች ውስጥ በመሠረታዊ አማርኛ ኮርሶች አሰጣጥ ወቅት የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተባበርን መፈተሽ ነው። አጥኚው የጥናቱን ተተኳሪዎች ለመምረጥ የግኝት ናሙና ዘዴን ተጠቅመዋል። በመቀጠልም ያልተደራጀ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የቪዲዮ ቀረጻ፣ ፎቶግራፍ፣ የጽሑፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻን በመጠቀም መረጃዎችን ከኮሌጁ አመራር አካላትና፣ ከተጠኙ መምህራንና ተማሪዎች ሰብስበዋል። የተገኘው ውጤትም በተጠኙ ኮሌጆች መሰረታዊ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስሶስት ክፍለ ጊዜያት ተዘውትሮ ሲተገበር ታይቷል የሚል ነው።

ደረጀ ነጋሽ (1999) "የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህረት ኮሌጅ የአማርኛ ትምህርት ክፍል በ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር" ነው።

የጥናቱ ዓላማ ኮሌጁ ለተጠኝነት በተመረጠው መርሃ ግብር የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተግባራዊ ያደረጉት ያልተደራጀ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የቪዲዮ ቀረፃ፣ የተማሪዎች የእለት ውሎ ማስታወሻ፣ የቃልና የጽሑፍ መጠይቅን ነው። የጥናቱን ተተኳሪዎች ለመምረጥ ስብጥራዊ፣ መጣኝና ዕጣ ማውጣት ናሙና ዘዴን ተጠቅመዋል። በዚህ መልክ የተገኘውን መረጃም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ትንተና አካሂደዋል። ከመረጃው የተገኘው ውጤትም የተማሪ ተኮር አቀራረብ በኮሌጁ ጥሩ በሚባል ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል የሚል ነው።

በአጠቃላይ የሙሉጌታ፣ ኢልያስና ደረጀ ስራዎች የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራን መፈተሻቸውና በከፊልም ቢሆን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጣ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስላቸው ነገር ግን እነዚህ ሥራዎች በኮሌጅ ደረጃ የተሰሩ፣ በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያልተደራጀ የክፍል ምልከታን (unstructured observation) የተጠቀሙ፣ መረጃዎችን ለመተንተን ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ብቻ የተከተሉና በመንግስታዊ የትምህርት ተቋማት ላይ ብቻ ያለውን የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ የፈተሹ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የዘመን፣ የመርሃግብር፣ የቦታ፣ የተጠኚዎች ብዛትና አይነት ወዘተ. ልዩነት ከመኖሩ በተጨማሪ ይህ ጥናት በዋና መረጃ መሰብሰቢያነት የተደራጀ ምልከታን /structured observation/፣ መረጃዎችን ለመተንተን አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን (Mixed Research Method) መከተሉ እንዲሁም የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶችን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር በመፈተሽና በማነጻጸሩ ከላይ ከተገለጹት ሥራዎች ልዩነት አላይቷል።

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው የአጠናን ዘዴ ዓይነታዊና መጠናዊ ምርምርን ሲሆን ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም በገለፃ መልክ ቀርቧል። የጥናቱም መረጃ የተሰበሰበው በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ አማካኝነት ነው። ይህን የሶስት ማዕዘናዊነት (triangulation) የመረጃ አሰባሰብ ሂደትን መከተል ያስፈለገውም የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ ነው።

### 3.1. የናሙና አመራረጥ

#### 3.1.1. የክልል አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ክልል ደብረታቦር ከተማ ሲሆን የክልል አመራረጡም የዓላማ ተኮር ናሙና (purposive sampling) ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም በሀገራችን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሁሉ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተግባራዊ እንዲሆን በመርህ ደረጃ ቢቀመጥም በክልሉ በሚገኙት በርካታ ትምህርት ቤቶች ግን የአፈጻጸም ችግር እንዳለ አጥኚዋ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ስብሰባዎች ሲነገር በመስማቷ ነው።

ደብረታቦር ከተማ ደግሞ በአማራ ክልል በመገኘቱና ለአጥኚዋ የሚፈለገውን መረጃ በቀላል መንገድ ለማግኘት በማስቻሉ የእመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ከተማው በተጠኚነት ተመርጧል።

#### 3.1.2. የትምህርት ቤት አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረታቦር ከተማ 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽና ማነጻጸር ነው። በከተማውም አምስት የመንግስትና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። በመሆኑም ከግል የዲቲ አካዳሚና ዳልሽህ ቤዛዊት አለም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጠቅላይ ናሙና /Comprehensive sampling/ መሠረት ተመርጠዋል። ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ የዳግማዊ ቴዎድሮስና ፊታአውራሪ ገብርየ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። ይህ የሆነበት ምክንያትም የግል ትምህርት ቤቶች ሁለት ብቻ ከመሆናቸው የተነሳ አመራጭ ባላመኖሩና የነዚሁ ትምህርት ቤቶች መምህራን ደግሞ አማርኛን በማስተማር ዘዴ የዲግሪ ምሩቃን

በመሆናቸው ነው። ስለሆነም አጥኝዋ የመንግስት ትምህርት ቤቶችን መምህራን ዳራ አሰሳ በምታካሂድበት ጊዜ ከሁለቱ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዲግሪ ምሩቅ መምህራን መኖራቸውን በማረጋገጧ ነው። ይህን ማድረግ ያስፈለገበትም በትምህርት ደረጃ ምክንያት ሊመጣ የሚችል ተለውጦን ለመቆጣጠር አመችነት ስላለው ነው።

### 3.1.3. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በደብረታቦር ከተማ ከሚገኙ የመንግስትና የግል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የዳግማዊ ቴዎድሮስ፣ ፊታአውራሪ ገብርየ፣ ዲቲ አካዳሚና ዳልሽህ ቤዛዊት አለም በተጠኝነት መመረጣቸው ተገልጿል። በመሆኑም አጥኝዋ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚመለከት ለማጥናት ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎችንም በመረጃ ሰጭነት ማሳተፍ የሚገኘውን ውጤት አስተማማኝነት ይጨምረዋል ብላ ታምናለች። ከዚህ በመነሳትም ከትምህርት ቤቱ የተሻለ የጊዜ ቆይታ ያላቸው የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆናቸው ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ከሚል እምነት በመነሳት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማዊ (Purposive Sampling Method) የአመራረጥ ሂደት በመረጃ ሰጭነት ሊመረጡ ችለዋል።

### 3.1.4. የመምህራን አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች በዳግማዊ ቴዎድሮስ አንድ ሴት፣ ፊታአውራሪ ገብርዬ አንድ ወንድ እንዲሁም ከግል ትምህርት ቤቶች ደግሞ በዲቲ አካዳሚ አንድ ወንድ እና በዳልሽህ ቤዛዊት አለም አንድ ወንድ በድምሩ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲኖሩ በጠቅላይ ናሙና (compressive sampling) መሠረት ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ያሉት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል።

### 3.1.5. የተማሪዎች አመራረጥ

በዚህ ጥናት የዳግማዊ ቴዎድሮስ፣ ፊታአውራሪ ገብርየ፣ ዲቲ አካዳሚና ዳልሽህ ቤዛዊት አለም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችም በመረጃ ሰጭነት ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል። በመሆኑም ከግል በዲቲ አካዳሚ 23፣ ዳልሽህ ቤዛዊት አለም 14 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በመገኘታቸውና በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች አንድ አንድ ምድብ ብቻ በመሆናቸው በጠቅላይ ናሙና ተመርጠዋል።

የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ስንመለከት ደግሞ በዳግማዊ ቴዎድሮስ 444 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን በ9 ምድብ ሲያስተናግድ፣ የፊታአውራሪ ገብርየ ትምህርት ቤት 301 ተማሪዎችን በ6 ምድብ ያስተናግዳል።

የዚህ ጥናት ትኩረትም የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽና ማነጻጸር በመሆኑና በተመረጡት ሁለት የመንግስትና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም አንድ፣ አንድ በድምሩ አራት ብቻ በመሆናቸው ከየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ ምድብ ማለትም ከዳግማዊ ቴዎድሮስ ምድብ "C"፣ ከፊታአውራሪ ገብርየ ምድብ "A"፣ ከዲቲ አካዳሚ ምድብ "A" ከዳልሽህ ቤዛዊት አለም የምድብ "A" ተማሪዎችን በመምረጥ በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል። የመንግስት ትምህርት ቤቶች የምድብ አመራረጥም የእጣ ናሙና ዘዴን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም የግል ትምህርት ቤቶች አማራጭ ምድብ ስለሌላቸው የክፍለ ጊዜ መደራረብን ለመቆጣጠር ሲባል ነው።

ሠንጠረዥ 1 የተመረጡ ተማሪዎች ዳራ

| ተ.ቁ | የሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ስም | የክፍል ደረጃና ምድብ | ፆታ | ብዛት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዳግማዊ ቴዎድሮስ* | 8ኛ C | ወ | 26 | 51 |
| | | | ሴ | 25 | |
| 2 | ፊታአውራሪ ገብርየ* | 8ኛ A | ወ | 22 | 49 |
| | | | ሴ | 27 | |
| 3 | ዲቲ አካዳሚ** | 8ኛ A | ወ | 10 | 23 |
| | | | ሴ | 13 | |
| 4 | ደልሽህ ቤዛዊት አለም** | 8ኛ A | ወ | 9 | 14 |
| | | | ሴ | 5 | |
| ድምር | | | | | 137 |

**መግለጫ**

* የመንግስት ትምህርት ቤት

** የግል ትምህርት ቤት

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.2.1. ምልከታ

ለዚህ ጥናት በዋናንት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ተግባር ላይ የዋለው ምልከታ ነው። "ምልከታ አጥኚው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው" (ያለው 2001፣182)።

በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ትኩረት ለሚያደርጉ ጥናቶች ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተመራጭና በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሊገኝ የማይችል ተፈጥሯዊ የሆነ የክፍል ውስጥ ድባብን የሚያሳይ በመሆኑ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ተመርጧል።

ይሁን እንጅ የምልከታ ዘዴ እንደ ጥናቱ ዓላማ ይወሰናል። ስለሆነም ለዚህ ጥናት ውስን ምልከታ /Fixed observation/ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተግባራዊ ተደርጓል። ይህ የምልከታ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም አጥኚዋ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ጊዜ በክፍል ውስጥ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል የጥናቱን ዓላማ ሊያሳኩ የሚችሉትን ነጥቦች መርጣ በማመሳከሪያ ሰነድ (check list) አማካኝነት ተግባራዊ አድርጋለች። ይህም የመምህራንን የክፍል ውስጥ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር በተወሰነ ጊዜና በተመጣጠነ ወጪ ተከታትሎ ለመገምገም የሚያስችል ሆኖ በመገኘቱ ነው። በዚህ የክፍል ውስጥ ምልከታም እያንዳንዱ መምህር ለአራት ተከታታይ ጊዜያት ታይቷል። ይሁን እንጅ ውጤት የተያዘው የሶስቱ ቀናት ብቻ ነው። ምክንያቱም ቀሪው አንድ ቀን መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ሊያሳዩ የሚችሉትን አዲስ ባህሪይ ለመቆጣጠር የማስመሰያ ምልከታ በመሆኑ በውጤቱ እንዳይካተት ተደርጓል።

በተጨማሪም የክፍል ምልከታው ውጤት የበለጠ አስተማማኝና ከአጥኚዋ ግላዊ አመለካከት የፀዳ እንዲሆን ስለተፈለገ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ እንዲታገዝ ተደርጓል።

-በመቅረጸ ምስል /Video camera/ ታግዟል። ይህ ቀረጻም የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግና እውናዊ የሆነውን የመምህራንና የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ክንውን ለማመሳከር ሲባል ለአራት ተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ተካሂዷል። ከዚህ ውስጥም የመጀመሪያው አንድ ቀን የማስመሰል ቀረጻ የተደረገበት ነው።

ሔአጥኘዋ በተጨማሪ አንድ የዲግሪ ምሩቅና 8 ዓመት የስራ ልምድ ያለው የአማርኛ ቋንቋ መምህር በረዳት መረጃ ሰብሳቢነት ተሳትፏል። ለረዳት መረጃ ሰብሳቢውም ስለ ማመሳከሪያ ሰነዱም ሆነ ስለአጠቃላይ ውጤት አሰጣጡ በቂ ገለጻ ተሰጥቶታል።

የማመሳከሪያ ሰነዱም አዎ (ተተግብሯል) ወይም የለም /አልተተገበረም/ የሚል በመሆኑ ከክፍል ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትም በአጥኝዋና ረዳት ሰብሳቢው አማካኝነት ከበቂ መረጃ ጋር ከተመዘገቡ በኋላ ክፍለ ጊዜው እንዳበቃ በአዲስ የማመሳከሪያ ሰነድ የየእለቱን ግምገማ በጋራ ውጤት የመስጠት ስራው እንዲከናወን ተደርጓል። በዚህ ወቅትም አለመግባባት በተፈጠረ ጊዜ በውይይት ስምምነት ላይ መደረስ ተችሏል።

በመጨረሻ ምልከታው እንደተጠናቀቀም በምልከታ ሰነዱ ጥያቄ አምስት ስለ ትምህርት ቤቶቹ አካባቢና የመማሪያ ክፍሎች ምቹነት ከተሰበሰበው መረጃ ውጪ በሁሉም ቀናት ከተሰበሰበው መረጃ የተገኘውን ውጤት በመደመር በሚከተለው ሁኔታ ዋጋ ተሰጥቶት ለትንተና ቀርቧል።

ምሳሌ፡- ጥያቄ (ነጥብ) አንድ 3 ቀን ሲተገበር 5 ነጥብ

2 ቀን ሲተገበር 4 ነጥብ

1 ቀን ሲተገበር 3 ነጥብ

ሳይተገበር ሲቀር ደግሞ 1 ነጥብ እንዲኖረው ተደርጓል።

ይህንን ማድረግ ያስፈለገበትም የጥናቱ ዋና ዓላማ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶችን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ማነጻጸር በመሆኑ ነው። ስለሆነም ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር አመሳክሮ ለማስቀመጥና የቲ-ቴስት ቀመርን ተጠቅሞ የተገኘውን የውጤት ልዩነት በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ነው።

### 3.2.2. የጽሑፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት የጽሁፍ መጠይቅ ዋና ዓላማ ከክፍል ምልከታው የተገኘውን ውጤት አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ነው። ስለሆነም በምልከታ የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያመች ዘንድ በማመሳከሪያ ሰነድነት

32

የቀረቡት ነጥቦች በተመሳሳይ ሁኔታ በመረጃ ሰጭነት ለተመረጡ ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅነት ተካትተው እንዲቀርቡ ተደርጓል።

ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የመላሾቹን አጠቃላይ መረጃ፤ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ በማመሳከሪያ ሰነዱ የተካተቱትና ስለመማር ማስተማሩ ሂደት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ዝግ ጥያቄዎች ናቸው። በሶስተኛው ክፍል የቀረቡት ግን በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ወቅት ተማሪዎች በቅርበት ሆነው ያዩትን ነገር ሁሉ በነጻነት የሚገልጹበት ልቅ (open ended) ጥያቄዎች ናቸው።

በማመሳከሪያ ሰነድነትም ሆነ በጽሑፍ መጠይቅነት የቀረቡት ነጥቦች ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ መልኩ በመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባር ላይ የዋሉ ናቸው። ሆኖም የዚህን ጥናት ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልክ በአጥኝዋ ከተዘጋጁ በኋላ በሁለት አማርኛ የማስተማር የ2ኛ ዲግሪ ተማሪዎችና በአማካሪ አስተያየት ዳብረው ስራ ላይ ውለዋል።

### 3.2.3. ቃለ መጠይቅ

በክፍል ምልከታው የተገኘውን ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ የተደራጀ ቃለመጠይቅ ተዘጋጅቶ ለመምህራን እንዲቀርብ ተደርጓል። የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችም ልክ እንደ ምልከታ ማመሳከሪያ ሰነዱና የጽሁፍ መጠይቁ ሁሉ በ2ኛ ዲግሪ ተማሪዎችና አማካሪ አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተስተካክለው ስራ ላይ ውለዋል።

በቃለ መጠይቁ የተካተቱት ጥያቄዎች በጽሑፍ መጠይቅና በምልከታ ማመሳከሪያ ሰነዱ የተዳሰሱንም ሆነ ያልተዳሰሱትን ጉዳዮች በማንሳት ሰፋት ያለውና የተብራራ ምላሽ ለማግኘት በሚያስችል ሁኔታ ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሆነዋል።

## 3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረታቦር ከተማ የሚገኙ ሁለት የግልና ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር መፈተሽና ማነጻጸር ነው። በመሆኑም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምልከታ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ

መጠይት ደግሞ አጋዥ መረጃ መሰብሰቢያዎች ናቸው። ስለሆነም በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች በወረቀት እንዲሰፍሩ ከተደረገ በኋላ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት ለየብቻው ተደምሮና አማካዩ ተሰልቶ ትንተናው ተካሂዷል። በትንተናው ወቅትም በአማካይ ውጤቶቹ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የቲ-ቴስት ስታትስቲካዊ ስሌት ተግባራዊ ተደርጓል። ለቀመሩም አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ማለትም በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን አማካይ፣ ልይይትና የነጻነት ደረጃ የመፈለግ ስራ ተሰርቷል። ከዚህ ቀጥሎም የልዩነት ደረጃውን ለማወቅ የቲ-ቴስት ውጤት (obtained value of t) ተሰልቶ ከስንጠረዥ ዋጋው /critical value of t/ ጋር ተነጻጽሯል። በንጽጽሩም በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን የልዩነት ደረጃ ጉልህ መሆንና አለመሆን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በሚደረግበት ወቅትም ለምንአልባት ስህተት 5%(P<0.05) በመተው ነው። በመረጃ ትንተናው ጊዜም በቃለ መጠይቅም ሆነ በተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተካተቱ (Open ended questions) እንዳስፈላጊነታቸው በማስገባት ትንተናው ተካሂዷል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው መረጃዎች በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል። እነዚህን መረጃዎችም በአራት ዋና ዋና ክፍሎች በመመደብ ትንተናው ተካሂዷል።

በመጀመሪያው ክፍል የተጠኝ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ፣ሁለተኛው ክፍል በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ ያለውን የመምህራንን ሚና የያዘ ሲሆን በስሩም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርቱ መግቢያ፣ በትምህርቱ ሂደት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንዲሁም የስነ-ዘዴ አጠቃቀማቸውን ሲያካትት፣ሶስተኛው ክፍል በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተማሪዎችን ሚና፣አራተኛው ክፍል ደግሞ የትምህርት ቤቱ አካባቢና የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለውን ምቹነት የያዘ ነው። እነዚህ ከሁለተኛው ጀምሮ የተገለጹት ነጥቦችም በየስራቸው የተለያዩ ንዑሳን ተግባራትን ያካተቱ ናቸው።

### 4.1. የተጠኝ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ

ትንተናውን ግልፅ ለማድረግ ያመች ዘንድ በጥናቱ የተካተቱ መምህራንና ተማሪዎችን ዳራ እንመለከታለን።

ሠንጠረዥ 2 የተጠኝ መምህራን ዳራ

| ተቁ | የሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ስም | የመምህራን ብዛት | እድሜ | የትምህርት ደረጃ | በአብይ የሰለጠኑበት የት/ት መስክ | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዳግማዊ ቴዎድሮስ | 1 | 47 | ዲግሪ | አማርኛ | 28 |
| 2 | ፊታውራሪ ገበርዬ | 1 | 48 | ዲግሪ | አማርኛ | 28 |
| 3 | ዲቲ አካዳሚ | 1 | 23 | ዲግሪ | አማርኛ | 4 |
| 4 | ዳልሽህ ቤዛዊት አለም | 1 | 23 | ዲግሪ | አማርኛ | 1 |

ከላይ ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሁሉም በአብይ ትምህርትነት የተማሩት አማርኛ ቋንቋን (በማስተማር ዘዴ) ሲሆን በትምህርት ዝግጅታቸውም የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው

ናቸው። ሌላው በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በእድሜ ገፋ ያሉ፣ ረዘም ላሉ ዓመታት ያስተማሩ መሆናቸውን ለመገመት ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በወጣትነት የእድሜ ደረጃ የሚገኙ እንዲሁም ለጥቂት ጊዜያት ያስተማሩ መሆናቸውን ለመረዳት ያስችላል።

ሠንጠረዥ 3 ለጥናቱ መረጃ የሰጡ (የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ) ተማሪዎች ዳራ

| ተ.ቁ | የሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ስም | እድሜ | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 13-16 | 17-20 | ከ 20 በላይ | |
| 1 | ዳግማዊ ቴዎድሮስ | 36 | 7 | 1 | 44 |
| 2 | ፊታአውራሪ ገብርየ | 36 | 8 | - | 44 |
| 3 | ዲቲ እኑዳሚ | 23 | - | - | 23 |
| 4 | ዳልሽህ ቤዛዊት አለም | 14 | - | - | 14 |
| | ድምር | 109 | 15 | 1 | 125 |

ከቀረበው መረጃ (ሠንጠረዥ 3) የተማሪዎችን ዳራ እንደምንረዳው የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት 125 ተማሪዎች መሆናቸውን ነው። ይህ የሆነበትም በምዕራፍ ሶስት እንደተጠቀሰው ለመረጃ ሰጭነት የተመረጡ ተማሪዎች ቁጥር 137 ቢሆንም በወቅቱ ተገኝተው መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ግን 125 ብቻ በመሆናቸው ነው። በመሆኑም ከግል ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ መረጃ ሰጭነት የተመረጡት ሁሉም በጥናቱ ተሳታፊ ሲሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ግን በዳግማዊ ቴዎድሮስ 7፣ በፊታአውራሪ ገብርየ ትምህርት ቤት ደግሞ 5 ተማሪዎች በወቅቱ ባለመገኘታቸው (ክፍል ውስጥ ባለመኖራቸው) በጥናቱ ተሳታፊ አልሆኑም።

ሌላው ከተማሪዎች ዳራ የምንረዳው መረጃ ከሰጡት ተማሪዎች መካከል 87.2% ያህሉ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን ነው። ይህም የተገኘዉ ዉጤት ከተማሪዎች የእድሜ ልዩነት (መራራቅ) አንፃር ለውጥ የማያስከትል ወይም የማይፈረጅ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። በእነዚህ ተማሪዎች የተሞሉ የጽሑፍ መጠይቆች መረጃም በጥንቃቄ እየተፈተሸ ወደ ወረቀት በሚሰፍርበት ጊዜ ምንም እንኳን በተለያዩ ጥቂት የጽሑፍ መጠይቆች ላይ መጠነኛ ግድፈት ቢታይም አናሳ በመሆኑና በጽሑፍ መጠይቁ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ባለመሆኑ መረጃው በስራ ላይ ውሏል።

## 4.2. በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የመምህሩ ተግባር (ሚና)

36

በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ መምህራን በትምህርቱ መግቢያ ተማሪዎችን ከፍዝ ተመልካችነት ወደ ንቁ ተሳታፊነት ለማሸጋገር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ የትምህርቱን ርዕስና ዓላማ ማስተዋወቅ፣ ትምህርቱን ከተማሪዎች የእለት ከእለት ተግባራት ጋር ማዛመድ፣ የተለያዩ ተግባራትን ማሰራትና ተከታትሎ ምጋቤ ምላሽ መስጠት፣ የተማሪዎችን የተለያየ የመማር ስልት በመለየትና የተማሪ ተኮር ስነ-ዘዴዎችን (መተግበሪያ መንገዶችን) መጠቀም ወዘተ. የመምህሩ ተግባር እንደሆነ ቀደም ሲል አይተናል በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ንዑስ ርዕስ (2.7.1) ይመልከቱ፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

### 4.2.1. በተማሪ ተኮር ትምህርት መግቢያ የመምህራን ሚና

በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር በትምህርቱ መግቢያ መምህራን ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል አራት ነጥቦች ተካትተዋል፡፡ እነርሱም የማነቃቂያ (መንደርደሪያ) ጥያቄዎችን /ሀሳቦችን/ ማቅረብ፣ የቤትና የክፍል ስራዎችን ተከታትሎ ምጋቤ ምላሽ መስጠት፣ የእለቱን ትምህርት ዓላማ ማስተዋወቅ እንዲሁም የእለቱን ትምህርት ከተማሪዎች የእለት ከእለት (የህይወት ልምድ) ጋር አዛምዶ ማቅረብ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ተግባራት መሠረት በማድረግ በክፍል ምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው ውጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ሰፍሯል፡፡

ሠንጠረዥ 4 በትምህርት መግቢያ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት

| ከምልከታ የተገኘ ውጤት | | | | | ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተጠኙ መምህራን | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት | የመረጃ ሰጭ ተማሪዎች | | አማካይ | ተ ቴስት | ጉልህ ልዩነት |
| ትምህርት ቤት | ብዛት | | | | ትምህርት ቤት | ብዛት | | | |
| የመንግስት | 2 | 4.125 | 1.397 | የለውም | የመንግስት | 88 | 4.364 | 0.062 | የለውም |
| የግል | 2 | 4.375 | | | የግል | 37 | 4.458 | | |
| የነፃነት ደረጃ 2<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 4.303 | | | | | የነፃነት ደረጃ 123<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 | | | | |

*P< 0.05

37

ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው በምልከታው ሂደት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን 4.125፣ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ደግሞ 4.375 አማካይ ውጤት ማስመዝገባቸውን ከተገኘው ውጤት ለመረዳት ተችሏል። በዚህ አማካይ ውጤት መሠረት በትምህርት መግቢያ አሰጣጥ ረገድ በመጠኑም ቢሆን የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካይ ውጤት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን አማካይ ውጤት የተሻለ ነው። ይሁን እንጅ ይህ የልዩነት ደረጃ የጎላ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያስችል ዘንድ በቲ-ስሌት ተፈትሾ የተገኘው ውጤት 1.397 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 4.303 መሆኑ ታውቋል። በዚህም የቲ-ቴስት ውጤቱ ከቲ-ስንጠረዥ ዋጋ (Critical value of t) ከበለጠ ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ ማለት ሲሆን ካነሰ ደግሞ ጉልህ የሆነ ልዩነት የለም የሚለውን ይገልጻል። ስለሆነም በምልከታ የተገኘው የግልና የመንግስት የመምህራን በትምህርት መግቢያ አንፃር የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ጉልህ ልዩነት እንዳላሳየ ለመረዳት ተችሏል።

በተመሳሳይ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተሰበሰበ መረጃ ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን 3.64፣ የግል 4.458 አማካይ ውጤት አግኝተዋል። በዚህ ውጤት መሠረት የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአንፃራዊ የተሻለ የትምህርት መግቢያ ትግበራ አላቸው። የተገኘውን አማካይ ውጤት በመያዝ በመካከላቸው ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገ የቲ-ስሌት የተገኘው የቲ-ቴስት ውጤት 0.062 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.960 በመሆኑ በመካከላቸው የተፈጠረው ልዩነት ጉልህ አለመሆኑ ታውቋል።

ይሁንና በምልከታው ወቅት እንደታየው የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቤትና የክፍል ስራዎችን ተከታትለው በማረም ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ግን በየተራ የተወሰኑ ተማሪዎችን ቁጥር በመጥራት መልስ እንዲሰጡ ሲያደርጉ ተስተውለዋል። በዚህም የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በትምህርት መግቢያ በመጠኑም ቢሆን የተሻለ የተማሪ ተኮር አተገባበር አሳይተዋል ወደሚል ድምዳሜ ሊደረስ ተችሏል። ሆኖም በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው አማካይ ውጤት አንፃራዊ በሆነ መልኩ የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሻለ የትምህርት መግቢያ አተገባበር አሳይተዋል ይባል እንጅ በግል

ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን እንከን የለሽ ናቸው ማለት ግን እንዳልሆነ ልብ ይሏል። ምክንያቱም በምልከታ ወቅት ለማየት እንደተሞከረው የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን በትምህርቱ መግቢያ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጽፈው ለተማሪዎች ሲያስተዋዉቁ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ግን ጭራሽን ለተማሪዎች በግልፅ የማያስተዋዉቁበት ጊዜም እንደነበር ለመረዳት ተችሏል።

### 4.2.2. በትምህርቱ ሂደት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሚና

በዚህ ንዑስ ስር መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማለትም ያልገባቸውን ጥያቄ እንዲጠይቁና እንዲመልሱ ማድረግ፣ በቡድን የማስተማር ዘዴ ጊዜ ተማሪዎችን በፆታና በችሎታ አሰባጥሮ ማስቀመጥ፣ የቡድን መሪ ማስመረጥና በክፍል ውስጥ የግልም ሆነ የቡድን ተግባራትን በሚሰጡበት ጊዜ በመዘዋወር አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል። በዚህ መሠረትም በምልከታና ለተማሪዎች በቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 5 በትምህርት ሂደቱ የመምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት

<table>
<tr><th colspan="5">ከምልከታ የተገኘ ውጤት</th><th colspan="5">ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት</th></tr>
<tr><th colspan="2">የተጠኙ መምህራን</th><th rowspan="2">አማካይ</th><th rowspan="2">ቲ ቴስት</th><th rowspan="2">ጉልህ ልዩነት</th><th colspan="2">የመረጃ ሰጭ ተማሪዎች</th><th rowspan="2">አማካይ</th><th rowspan="2">ቲ ቴስት</th><th rowspan="2">ጉልህ ልዩነት</th></tr>
<tr><th>ትምህርት ቤት</th><th>ብዛት</th><th>ትምህርት ቤት</th><th>ብዛት</th></tr>
<tr><td>የመንግስት</td><td>2</td><td>3.875</td><td rowspan="2">1.397</td><td rowspan="2">የለውም</td><td>የመንግስት</td><td>88</td><td>3.938</td><td rowspan="2">0.263</td><td rowspan="2">የለውም</td></tr>
<tr><td>የግል</td><td>2</td><td>4.125</td><td>የግል</td><td>37</td><td>4.246</td></tr>
<tr><td colspan="5">የነፃነት ደረጃ 2<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 4.303</td><td colspan="5">የነፃነት ደረጃ 123<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 1.960</td></tr>
</table>

*P< 0.05

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በክፍል ምልከታው የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን 3.875፣ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ደግሞ 4.125 አግኝተዋል። ከዚህ አማካይ ውጤት የምንረዳው በመጠኑም ቢሆን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይልቅ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በትምህርቱ ሂደት የተሻለ የተማሪ

ተኮር ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው ነው። ሆኖም ልዩነቱ የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በቲ-ስሌት በሚረጋገጥበት ጊዜ የቲ-ቴስት ውጤቱ 1.397 ሲሆን የቲ-የሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 4.303 በመሆኑ በምልከታ በተገኘው ውጤት ጉልህ የሆነ ልዩነት እንዳልተፈጠረ ታውቋል።

ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘ አማካይ ውጤት ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን 3.938፣ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን 4.246 አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። በጽሑፍ መጠይቁም በአንፃራዊ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በትምህርቱ ሂደት የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። ይሁን እንጂ በዚህ ውጤት አማካኝነት በተገኘው መረጃ የተፈጠረውን የልዩነት ደረጃ ምን ያህልነት ለማወቅ በተደረገው የቲ-ስሌት መሰረት የተመዘገበው የቲ-ቴስት ውጤት 0.263 ሲሆን የቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.960 ነው። ስለሆነም የቲ-ቴስት ውጤቱን ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በምናነጻጽርበት ጊዜ የቲ-ቴስቱ ውጤት አንሶ በመገኘቱ በመካከላቸው የተከሰተው የልዩነት ደረጃ ጉልህ አለመሆኑ ተረጋግጧል። ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በምልከታም ሆነ በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ መሰረት በተገኘው አማካይ ውጤት የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በመጠኑም ቢሆን የተሻለ አተገባበር አሳይተዋል ለማለት አስችሏል።

ይህም ሊሆን የቻለው በክፍል ምልከታው ለማረጋገጥ እንደተሞከረው የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የክፍል ስራዎችን በሚሰጡበት ጊዜ በሁሉም ተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድግ ሁሉም ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁም ሆነ እንዲመልሱ ሲያበረታቱ ተስተውለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉንም ቡድን እኩል ተዘዋውሮ ድጋፍ አለማድረግ፣ በቁጥር የተወሰኑ ተማሪዎችን በመጥራት ማሳተፍ እንጂ ለእያንዳንዱ ተማሪ እድል ሰጥተው ሲያሳትፉ አለመታየትና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከላይ እንደተገለጸው በተማሪ ተኮር ትግበራ የትምህርት ሂደት ጊዜ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በመጠኑ የተሻሉ መሆናቸው ታይቷል።ይሁን እንጂ በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝቱ (2.6.2.3) እንደተገለጸው መምህራን በቡድን የማስተማር ዘዴ ጊዜ ተማሪዎችን በፆታና በችሎታ አሰባጥረው ማደራጀትና የቡድን መሪ ማስመረጥ የየራሳቸው የሆነ ጠንካራ ጎን እንዳላቸው ተገልጿል። ነገር ግን በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን

በቡድን ሲያደራጁ የፆታና የችሎታ ስብጥርን እንደማይጠቀሙና የቡድን መሪም እንደማያስመርጡ በተደረገው ምልከታ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ችግር በተለይ በአንደኛው የግል ትምህርት ቤት ጎልቶ ይታይ ነበር። በዚህ ጉዳይም ከመምህሩ መረጃ ለማግኘት በተደረገው ቃለ መጠይቅ "እኔ በቡድን በማስተምርበት ጊዜ ተማሪዎች በፆታና በችሎታ እንዲሰባጠሩ ፍላጎቱ አለኝ፤ ብዙ ጊዜም በዚህ ጉዳይ ተማሪዎችን ለመምከር ሞክሬ ነበር፤ ነገር ግን በተለይ ሴት ተማሪዎች በፆታ ተሰባጥረው ለመቀመጥ ደስተኞች አይደሉም" በማለት ገልፀዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለም ለተማሪዎች በቀረበው ልቅ ጥያቄ (Open ended Questions) የተወሰኑ ወንድ ተማሪዎች ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ አስተያየት ሲሰጡ "ከጓደኞቻችን ጋር ተመራርጠን ስለምንቀመጥና ስለምናወራ ትምህርታችን በአግባቡ እየተማርን አይደለም ስለዚህ በፆታና በትምህርት ችሎታ ተሰባጥረን ብንቀመጥ ጥሩ ነው" ሲሉ በዚህ ጉዳይ ሴት ተማሪዎች ግን ምንም አይነት አስተያየት አለመስጠታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

### 4.2.3. የመምህሩ የተማሪ ተኮር ትምህርት ስነ-ዘዴ አተገባበር

በዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ዋና የተባሉ የተማሪ ተኮር ትምህርት ዘዴዎች (የማስተማሪያ መንገዶች) ማለትም በግል የመማር ዘዴ፣ በቡድን የማስተማር ዘዴ፣ ችግርፈች ዘዴ፣ የሚና ጨዋታና በፕሮጀክት ስራ የማስተማር ዘዴ የሚሉት ተካትተዋል የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት (2.6) ይመልከቱ ።

ሠንጠረዥ 6 **የመምህሩ የተማሪ ተኮር ትምህርት የስነ ዘዴ አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት**

| ከምልከታ የተገኘ ውጤት | | | | | ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተጠኑ መምህራን | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት | የመረጃ ሰጭ ተማሪዎች | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት |
| ትምህርት ቤት | ብዛት | | | | ትምህርት ቤት | ብዛት | | | |
| የመንግስት | 2 | 2.3 | 1 | የለውም | የመንግስት | 88 | 3.15 | 0.259 | የለውም |
| የግል | 2 | 2.2 | | | የግል | 37 | 3.493 | | |
| የነፃነት ደረጃ 2<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 4.303 | | | | | የነፃነት ደረጃ 123<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 | | | | |

*$P < 0.05$

ከመረጃው እንደሚታየው በምልከታ በተገኘው ውጤት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን በአማካይ 2.3 ሲያስመዘግቡ በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ደግሞ 2.2 አስመዝግበዋል። በዚህ ውጤት መሠረትም የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመጠኑ የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት ስነ-ዘዴ አተገባበር እንዳላቸው ታይቷል። ይሁን እንጅ የልዩነቱን ደረጃ ጉልህ መሆንና አለመሆን ለማረጋገጥ በተደረገው የቲ-ስሌት መሠረት የቲ-ቴስት ውጤቱ 1 ሲሆን የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋው ደግሞ 4.303 በመሆኑና የቲ-ቴስቱ ውጤት ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ በማነሱ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ ታውቋል።

በተመሳሳይ ለተማሪዎች በቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤቶች 3.15 አማካይ ውጤት ሲያገኙ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን 3.493 አግኝተዋል። ከዚህ መረጃ በተገኘው ውጤት ደግሞ በአንፃራዊ ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ይልቅ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተሻለ የተማሪ ተኮር ስነ-ዘዴ አተገባበር እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። የልዩነቱን ደረጃ ጉልህ መሆንና አለመሆን ለማወቅ በተደረገው የቲ-ስሌትም የቲ-ቴስት ውጤት 0.259 ሲሆን የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.960 በመሆኑ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል።

ከላይ የተገኘውን የመረጃ ውጤት ጠቅለል አድርገን በምናይበት ጊዜ በምልከታ በተገኘው ውጤት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን በመጠኑ የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት የስነ-ዘዴ አተገባበር አስመዝግበዋል። ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ደግሞ በአንፃራዊ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የተሻለ የስነ-ዘዴ አተገባበር እንዳላቸው ያስረዳል።

ይሁን እንጅ ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ሊተገብሩ በብዛት የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች (ስነ-ዘዴዎች) በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን መልስ "የግልና የቡድን ማስተማር ዘዴን" የሚል ነው (አባሪ 6) ይመልከቷል። ይህም የተገለጹትን ዘዴዎች ብቻ እንደሚጠቀሙ ለመረዳት አያዳግትም። ነገር ግን ከላይ ለተለገጸው የውጤት ልዩነት መንስኤ የሆነው በምልከታ ወቅት በዳግማዊ ቴዎድሮስ ትምህርት ቤት የሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ መምህር የተማሪ ችግሮች ናቸው ያሏቸውን ነቅሰው በማውጣትና ለተለያዩ ቡድኖች የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት

ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው በመረው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ማድረጋቸው ነው። መምህሯ ካቀረቧቸው የመወያያ ነጥቦች መካከልም የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. አያንዳንዱ ተማሪ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የማያመጣው ለምንድን ነው? ይህን ችግርስ እንዴት ማቃለል ይቻላል?

2. ተማሪ የቤት ስራ ሳይሰራ የሚመጣው ለምንድን ነው? ይህስ እንዴት ሊቃለል ይችላል? እና የመሳሰሉትን በማንሳት ተማሪዎች የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ተወያይተው እንዲፈቱ ሲያደርጉ በመታየታቸው ምክንያት ነው።

በአጠቃላይ ግን የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት ስነ-ዘዴ አተገባበርን አማካይ ውጤት በምናይበት ጊዜ ዝቅተኛ ነው። ምክንያቱም የግልና የቡድን የማስተማር ዘዴዎች የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳላቸውና እዚህን ዘዴዎች ብቻ መጠቀሙ ደግሞ የተለያዩ ተማሪዎችን የመማር ስልት ማዕከል ያደረገ አለመሆኑን ያስረዳል የተዛማጅ ጽሁፉ (2.6.1.2) እና (2.6.2.4) ይመልከቱ። ሆኖም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከመንግስትም ሆነ ከግል ትምህርት ቤቶች በምልከታና በጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው አማካይ ውጤት በጣም ዝቅተኛ የሚባል ሲሆን ከመካከላቸው የተፈጠረውን የልዩነት ደረጃ ለማወቅ በተደረገው የቲ-ቴስት ስሌትም ጉልህ ልዩነት እንዳልታየ ለማወቅ ተችሏል። ይሁን እንጅ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የተለያዩ የተማሪ ተኮር ስነ ዘዴዎችን (መተግበሪያ መንገዶችን) አፈራርቀው መጠቀም ሳለመቻላቸው ምክንያት የሚከተሉትን ገልጸዋል።

የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን "ትምህርት ቤቱ የመማሪያ መፃሕፍትን እንደ መንግስት ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች አያድልም። በመሆኑም ሁሉም ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉ በእጃቸው የለም። በዚህ የተነሳ የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ስነ ዘዴዎችን እንዳ አስፈላጊነታቸው ለመጠቀም ገድቦናል" በማለት መልሰዋል።

ሌላውና ለተማሪ ተኮር ትምህርት ስነ ዘዴዎች ትግበራ እንደመሰናክል የታየው መምህራን " የመማሪያ መፅሐፉ ይዘት ሳቢና ማራኪ አይደለም፤ በመሆኑም ተማሪዎች እንዲወያዩ በሚሰጣቸው ትምህርታዊ ይዘቶች ላይ ከመወያየት ይልቅ ሌሎች ተግባራትን ሲያከናዉኑ ይታያሉ ይህም የመፅሐፍ ዝግጅቱ ያመጣው ችግር ነው።" በማለት አክለውም የመፅሐፉ

የደበት ምጣኔም ችግር ይታይበታል። ይህ ደግሞ የመጽሐፉን ይዘት ለመሸፈንና በንመታዊ እቅዱ ለመመራት ስንል ከግልና ከቡድን የማስተማሪያ ዘዴዎች በተጨማሪ የመምህር መራሹን ዘዴ እንድንጠቀም ያስገድደናል በማለት ገልጸዋል። ሌላውና ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ከቃለ መጠይቁ ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወስደው ከሆነስ ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ቢገልጹኝ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ለሶስት ጊዜ ያህልና ለአንድ አንድ ቀን በማለት ሲመልሱ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ግን በትምህርት ላይ ሳሉ ከወሰዷቸው "ኮርሶች" ውጭ በስራ ዓለም የስልጠና እድሉ እንዳልገጠማቸው ገልጸዋል (አባሪ 6) ይመልከቱ። በመሆኑም አንዱ ምክንያት የስራ ላይ ስልጠና አለማግኘትና አጥጋቢ አለመሆንም ጭምር መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

## 4.3. በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ (ሚና)

በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የተማሪዎች ተሳትፎ /ሚና/ በትምህርት ሰዓት ፍዝ ተመልካች ከመሆን ይልቅ በንቃት መሳተፍ፣ በትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ሀላፊነትን መቀበልና የእኔነት ስሜት መፍጠር፣ ከመምህሩ ጋር በመተባበር የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን መምረጥና የተሰሩ ተግባራትን በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሪፖርት ማድረግ ወዘተ. እንደሚያጠቃልል ተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት (2.7.2) ይመልከቱ።

በመሆኑም በዚህ ንዑስ ስር ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት፣ መግለጽ፣ ለንግግር፣ ክርክር ወይም ውይይት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮችን መምረጥና መከራከር፣ ንግግር ማድረግ ወይም መወያየት እንዲሁም የተሰጡ ተግባራትን በሪፖርት መልክ ማቅረብ የሚሉት ይገኙበታል።

ሠንጠረዥ 7 በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተማሪዎች ሚና (ተሳትፎ) የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት

| ከምልከታ የተገኘ ውጤት | | | | | ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተጠኙ መምህራን | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት | የመረጃ ሰጭ ተማሪዎች | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት |
| ትምህርት ቤት | ብዛት | | | | ትምህርት ቤት | ብዛት | | | |
| የመንግስት | 2 | 4.00 | 0.982 | የለውም | የመንግስት | 88 | 4.438 | 0.129 | የለውም |
| የግል | 2 | 4.167 | | | የግል | 37 | 4.639 | | |
| የነፃነት ደረጃ 2<br>የስንጠረዥ ዋጋ 4.303 | | | | | የነፃነት ደረጃ 123<br>የስንጠረዥ ዋጋ 1.960 | | | | |

$^*P < 0.05$

ከላይ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው ከምልከታ የተገኘው ውጤት በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች 4.00፣ በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ 4.167 አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። በመሆኑም በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ ተማሪዎች ይልቅ በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በመጠኑም ቢሆን በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተሻለ እንቅስቃሴ (ተሳትፎ) እንዳላቸው ያሳያል። ስለሆነም ልዩነቱ የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በተደረገው የቲ-ስሌት የተገኘው የቲ-ቴስት ውጤት 0.982 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 4.303 በመሆኑ በአማካይ ውጤቱ መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ እንዳልሆነ ተመልክተናል።

ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ከተገኘ መረጃ ደግሞ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች 4.438፣ በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች 4.639 አማካይ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህን ውጤት መሰረት በማድረግም በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ወቅት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ይልቅ በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርታዊ ተሳትፎ በአንፃራዊ የተሻለ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል። ይሁን እንጅ በአማካይ ውጤቱ የተከሰተውን የልዩነት መጠን ምን ያህልነት ለማወቅ በተደረገው የቲ-ስሌት ፍተሻ የተገኘው የቲ-ቴስት ውጤት 0.129 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.960 ሆኖ በመገኘቱ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ በቲ-ቴስቱ ስሌት ጉልህ የሆነ ልዩነት አይታይእንጅ በምልከታም ሆነ በጽሑፍ መጠይቅ በተገኘ አማካይ ውጤት በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በመጠኑ

የተሻለ ትምህርታዊ ተሳትፎ አሳይተዋል። ለዚህ ውጤትም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በምልከታ ወቅት በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የተለያዩ ተግባራትን ለመስጠት ሲፈልጉ የተማሪዎችን ፈቃድ መጠየቅና የማግባባት ስራ መስራት፣ የመከራከሪያ ርዕሶችን ተማሪዎች በራሳቸው እንዲመርጡ ማድረግና ጥያቄ እንዲጠይቁ የማመቻቸት ወዘተ. ተግባራትን በማድረጋቸው ተማሪዎችም ሙሉ በሙሉ የተሠጣቸውን እድል ሲጠቀሙበት ተስተውሏል።

ምሳሌ፡- ዳልሽህ ቤዛዊት እለም ከተባለው የግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት መምህር ተማሪዎችን የመከራከሪያ ርዕስ እንዲመርጡ አደረጉ። በዚህ ጊዜ ተማሪዎችም ከገበሬና ነጋዴ ማን ይበልጣል? የሚል መከራከሪያ ርዕስ፣ ዳኞችና ፀሀፊም መረጡ። ዳኞቹና ፀሐፊዋ የሚያከናውኑት ተግባር እንዲሁም ተከራካሪዎች የክርክር ሂደትን ተከትለው የሚያደርጉት ክርክርና የተቃራኒ ቡድኖችን ጥያቄ ለመመለስም ሆነ ለመጠየቅ ያላቸው ፍላጎት በመጠኑም ቢሆን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የተሻለ ነበር። ይህ ሊሆን የቻለበትም መምህሩ ለተማሪዎች የወንድማዊ ፍቅርና ፈገግታ በማሳየታቸው ተማሪዎችን በነፃነት እንዲሳተፉ አድርገዋቸዋል ብሎ ለመገመት ያስችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በምልከታው ለማረጋገጥ እንደተሞከረው የመንግስት ትምህርት ቤቶችን መምህራን ስናይ ተማሪዎችን የማቅረብ ስራ አይሰሩም። ተማሪዎችም መምህሮቻቸውን ከማክበር ባለፈ ሁኔታ ሲፈሯቸው ይስተዋላሉ። መምህራንም የክፍል ውስጥ ተግባራትን በትዕዛዝ መልክ የመስጠት፣ የመወያያ ርዕስ መምህሩ በራሳቸው መርጠው ለየቡድኑ ማደልና እንዲወያዩበትና (እንዲከራከሩበት) የማድረግ ወዘተ. ትግበራ ታይቷል። በዚህ ጊዜም ተማሪዎቹ የውይይትና ክርክር ስርዓትን ወይም መስፈርትን የተከተለ አካሄድ አልነበራቸውም። ከዚህ በተጨማሪም ሀሳባቸውን ለመግለጽ እድል ያገኙ ተማሪዎች እንኳን ሀሳባቸውን በነፃነት አብራርተው ሲገልጹ አልተስተዋሉም።

## 4.4. ትምህርት ቤቱና የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው ምቹነት

የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን በሚመች አካባቢና በተደራጀ የመማሪያ ክፍል ማስተማር ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ለማድረግ እንደሚያስችል በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝቱ (2.4)፣ የመማሪያ ክፍሉች፣ የተማሪዎች ቁጥር አለመመጣጠንና አካባቢና

ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ደግሞ (2.8.6) እና (2.8.7) ይመልከቱ። 46

ስለሆነም በዚህ ንዑስ ስር የትምህርት ቤቱ አካባቢና የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው ምቹነት፣ በክፍሉ በቂ ብርሃን መኖሩን፣ ወለሉን፣ ወንበሩን፣ ጥቁር ሰሌዳውን፣ የበሩንና መስኮቱን ምቹ መሆን አለመሆን ወዘተ. ያጠቃልላል።

ሠንጠረዥ 8 ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ትምህርት ቤቱና የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው ምቹነት የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት

| ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የመረጃ ሰጭ ተማሪዎች | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት |
| ትምህርት ቤት | ብዛት | | | |
| የመንግስት | 88 | 3.887 | 4.167 | አለው |
| የግል | 37 | 4.412 | | |
| የነፃነት ደረጃ 123 | | | | |
| የሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 | | | | |

*P < 0.05

በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ እንደምንመለከተው ለተማሪዎች በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ከመንግስት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ተማሪዎች የተገኘው አማካይ ውጤት 3.887 ሲሆን በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ከሞሉት የፅሑፍ መጠይቅ ደግሞ 4.412 አማካይ ውጤት ተገኝቷል። በመሆኑም ከተገኘው አማካይ ውጤት የግል ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የተሻለ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል። በአማካይ ውጤቱ የታየው ልዩነትም በቲ-ስሌት አማካኝነት በተደረገው ፍተሻ የቲ-ቴስት ውጤት 4.167 ሲሆን የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.960 በመሆኑ ጉልህ የልዩነት ደረጃ መኖሩን አሳይቷል።

በምልከታ በተገኘው ውጤትም የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተቆረቆሩበት አካባቢ ለትምህርት ትግበራ ምቹ ይሁን እንጅ የሁለቱንም ተቋማት የመማሪያ ክፍሎች በምናይበት ጊዜ ልዩነት መኖሩን ተመልክተናል። በምልከታው ወቅትም የግል ትምህርት ቤቶች በሮችና መስኮቶች እንዲሁም ወለል የተሟሉና የተስተካከሉ ሲሆን የመንግስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ አንደኛው ትምህርት ቤት ሁሉ ነገሩ ተሟልቶ በር

ያልተገበሙለት ነው። ሌላው ደግሞ መስኮቶቹ በጣም ሰፋፊና የቆርቆሮ ከመሆናቸው የተነሳ ሲዘጉ ይጨልማል፤ ሲከፈቱ ደግሞ በጧቱ ፈረቃ ፀሀይ በመግባት ከተማሪዎች ደብተር ያርፍና ለመፃፍ ያስቸግራል፤ ግድግዳውም የጭቃ ሆኖ የተቀባው ቀለም ተፋፍቶ አፈሩ የወጣ፤ እንዲሁም ወለሉ ልሾ ባለመሆኑ አቧራው አስቸጋሪ የሆነ ነው። ክፍል ውስጥ ካሉት ወንበሮች መካከልም የተወሰኑት ማስደገፊያቸውና መቀመጫቸው የተለያዩ "ዴስኮች" በመሆናቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ችግር ሲፈጥሩ ተስተውለዋል (አባሪ 7) ይመልከቱ። በመሆኑም የግል ትምህርት ቤቶች የክፍል ግንባታ ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የተሻሉና ጤናማ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማከናወንም ሆነ የተማሪ ተኮር ትምህርትን ለመተግበር የሚያስችሉ ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ ከምልከታና ከጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው ውጤት የግል የትምህርት ቤቶች ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ምቹ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

ሠንጠረዥ 9 የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አጠቃላይ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር የአማካይና የቲ-ቴስት ውጤት

| ከምልከታ የተገኘ ውጤት | | | | | ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተጠኑ መምህራን | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት | የመረጃ ሰጭ ተማሪዎች | | አማካይ | ቲ ቴስት | ጉልህ ልዩነት |
| ትምህርት ቤት | ብዛት | | | | ትምህርት ቤት | ብዛት | | | |
| የመንግስት | 2 | 3.575 | 0.087 | የለውም | የመንግስት | 88 | 3.955 | 0.505 | የለውም |
| የግል | 2 | 3.717 | | | የግል | 37 | 4.249 | | |
| የነፃነት ደረጃ 2<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 4.303 | | | | | የነፃነት ደረጃ 123<br>የሰንጠረዥ ዋጋ 1.960 | | | | |

*P < 0.05

ጠቅለል ባለመልኩ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ እንደምንረዳው በምልከታ በተገኘው መረጃ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን 3.575 ሲያገኙ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት ደግሞ 3.717 አስመዝግበዋል። በዚህ ውጤት መሠረትም የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በአንፃራዊ የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። ይሁን እንጂ የልዩነት ደረጃውን ለማወቅ በተደረገ የቲ-ስሌት የቲ-ቴስት ዋጋው 0.087 ሲሆን የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 4.303 በመሆኑ የልዩነት ደረጃው ጉልህ እንዳልሆነ ተረጋግጧል።

ከተማሪዎች በተሰበሰበ የጽሑፍ መጠይቅም የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን 3.955 ሲያስመዘግቡ የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ደግሞ 4.249 አስመዝግበዋል። በዚህ ውጤትም የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን በመጠኑም ቢሆን የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ አሳይተዋል። ሆኖም የልዩነት ደረጃውን ለማወቅ በተደረገ የቲ-ስሌት ቀመር ግን የቲ-ቴስት ዋጋ 0.505 ሲሆን የቲ-ስንጠረዥ ዋጋ 1.960 በመሆኑም ጉልህ የሆነ ልዩነት እንዳልታየ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ በምልከታም ሆነ በፅሑፍ መጠይቁ የተገኘው ውጤት ሲታይ የጎላ ልዩነት አይታይ እንጅ በተገኘው አማካይ ውጤት የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ አላቸው ለማለት ይቻላል። ለዚህም እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሰው የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን የቅርብ ዓመታት ተመራቂዎችና አፍላ የእድሜ ደረጃ ላይ ያሉ፣ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ፣ የመማሪያ ክፍሎቹም የተሟሉና ንፅህናቸው ለተስተምሮ ሂደት ምቹ የሆኑ ወዘተ. መሆናቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ከግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋር ሲነጻጸሩ ለረጅም አመታት በስራ ላይ የቆዩ፣ ከያዙት የትምህርት ደረጃ በሂደት የደረሱ መሆናቸውና በመጠኑም ቢሆን ከግል ትምህርት ቤቶች መምህራን አንፃር ሲታዩ ከዲሞክራሲያዊነት ይልቅ ኢ-ዲሞክራሲያዊነት የሚታይባቸው ናቸው። ሌላው የመንግስት ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች ከግል ትምህርት ቤቶች ጋር ሲተያዩም ችግር ያለባቸው መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረታቦር ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች የፀኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽና ማነጻጸር ነው። በዚህ ዋና ዓላማ ስርም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይገኛሉ።

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ፤
- በተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር አንዱ ትምህርት ቤት ከሌላው ትምህርት ቤት የሚሻልበት ሁኔታ ካለ ማየትና ምክንያቱንም ማረጋገጥ፤
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ ተኮር ዘዴን ለመተግበር እንደ ችግር የሚነሱ ጉዳዮችን መለየትና የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም የሚሉት ይገኙበታል።

ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስም በጥናቱ ዳራ 1.1 ላይ የተነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መልሷል።

### 5.1. ማጠቃለያ

በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ የመምህራን የትምህርት መግቢያ አሰጣጥ፤ በትምህርቱ ሂደት ያላቸው አተገባበር እንዲሁም በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ወቅት የተማሪዎችን ተሳትፎ በምናይበት ጊዜ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ ትግበራና ተሳትፎ ቢሆንም የልዩነት ደረጃውን ለማወቅ በተደረገው የቲ-ቴስት ስሌት ግን ልዩነቱ የጎላ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል።


በመምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት የስነ ዘዴ አተገባበር ደግሞ በምልከታ የተገኘው አማካይ ውጤት የመንግስት ትምህርት ቤቶች በአንፃራዊ የተሻለ ትግበራ ሲያሳዩ ከተማሪዎች በተገኘ የጽሑፍ መጠይቅ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሻለ ትግበራ እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል። ይሁን እንጅ

በምልከታም ሆነ በጽሑፍ መጠይቁ በተገኘው አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት በቲ-ቴስት ሲሰላ ጉልህ እንዳልሆነ ተረጋግጧል።

ሌላው በትምህርት ቤትና የመማሪያ ክፍሉቹ ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያላቸውን አመችነት በምናይበት ጊዜ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው አማካይ ውጤት የግል ትምህርት ቤቶች የተሻለ የመማሪያ ክፍል ግንባታ ስላላቸው ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ አመች ሆነው ተገኝተዋል። ይህን አማካይ ውጤትም በቲ-ቴስት ሲሰላ ጉልህ ልዩነት እንዳለ ለመረዳት ተችሏል።


ይህም በምልከታ እንደተረጋገጠው ሁሉም ትምህርት ቤቶች የትምህርት ሂደት አመችነት ካላቸው አካባቢዎች የተቆረቆሩ ቢሆኑም የመንግስት ትምህርት ቤቶች የክፍል ግንባታ፣ በሮች መስኮቶች ወለልና ግድግዳ እንዲሁም ወንበሮች ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ አመችነት የሌላቸው ሲሆኑ የግል ትምህርት ቤቶች ግን የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል። የተገኘውንም ውጤት በሚከተለው አኳኋን በግራፍ ማጠቃለል ይቻላል።

1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ




ከዚህ መረጃ የምንረዳው በስነ-ዘዴ አተገባበር የመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአንጻራዊ የተሻለ የተማሪ ተኮር ትግበራ ሲያሳዩ በሌሎች ተግባራት ግን በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን በመጠኑም ቢሆን የተሻሉ መሆናቸውን ነው።

2. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ




ከዚህ ግራፍ የምንረዳው ደግሞ በመጠኑም ቢሆን በሁሉም ተግባራት የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ማሳየታቸውን ነው።

በአጠቃላይ በግራፎቹ እንደተገለጸው በምልከታም ሆነ በጽሑፍ መጠይቅ ከተሰበሰበው የመረጃ ውጤት መረዳት እንደተቻለው በአብዛኛው በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር እንዳላቸው ያስረዳል። ይሁን እንጂ የአጠቃላይ ተግባራት አማካይ ውጤት ተደምሮና ጠቅላላ አማካዩ ተሰልቶ በሠንጠረዥ 9 እደተገለጸው የተገኘው አማካይ ውጤት በመጠኑ ልዩነት ቢኖረውም በቲ-ቴስት ስሌት ሲሰላ ግን በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ላይ ጉልህ የሆነ የልዩነት ደረጃ እንዳልተፈጠረ ተረጋግጧል። በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር መካከል ያለው የልዩነት ደረጃ ጉልህ ባይሆንም ለአማካይ ውጤቱ ልዩነት መከሰት በምክንያትነት የሚጠቀሱት ጉዳዮች ግን የሚከተሉት መሆናቸው በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

- የመምህራን የሥራ ላይ ስልጠና አለመስጠትና የተሰጡ ስልጠናዎችም አጥጋቢ አለመሆን፣

52

- የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን በክፍልም ሆነ በቤት ስራ መልክ የሚሰጧቸውን ተግባራት በትዕዛዝ መልክ ሲያስተላልፉ፣ የግል ትምህርትቤቶች መምህራን ደግሞ ለተማሪዎች በምርጫ መልክ በማቅረብ የማግባባትና ስምምነት ላይ የመድረስ ሁኔታ መኖር፣
- በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት ለመናገር የሚቸገሩና የሚፈሩ ሲሆኑ የግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ደግሞ በመጠኑም ቢሆን በነፃነት መናገር የሚችሉ መሆናቸው፣
- በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ዘንድ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት ወቅት የርዕስ አመራረጥና የይዘት ምጣኔ የተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራን ከግንዛቤ ያስገባ አይደለም የሚል እምነት መኖር፣
- በግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ብዙሀኑ ተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ስለሌላቸው መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን በአግባቡ ለመተግበር ተቸግረናል ማለታቸው፣
- የመንግስት ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ክፍሎች በር፣ መስኮትና ወለል ወዘተ. ችግር የሚታይባቸው ሲሆኑ በአንፃራዊ የግል ትምህርት ቤቶች ግን የተሻሉ በመሆናቸውና
- በመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተማሪዎች ቁጥር ብዙ ስለሆነ የተለያዩ ተግባራትን ለማሠራትና እያንዳንዱን ተማሪ ለማሳተፍም ሆነ ለመገምገም አንችልም ብለው ማመናቸው የሚሉት ናቸው።

ከላይ የተገለጹትና ሌሎችም ችግሮች የመንግስትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ጊዜ የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን ለመተግበርም ሆነ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው ለመረዳት ተችሏል።

## 5.2. አስተያየት

የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች በአስተያየት መልክ ቀርበዋል።

- መምህራን ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ስልጠና ቢወስዱ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለሚገጥሟቸው ችግሮች ሁሉ በቀላሉ የመፍትሄ ርምጃ ለመውሰድና የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን ለመተግበር ስለሚያግዛቸው በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን አጥጋቢ የሆነ የስራ ላይ ስልጠና ቢሰጣቸው፣
- የግል ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ እያለ የግልና የቡድን ማስተማር ዘዴን ብቻ እንደሚጠቀሙ በምልከታውና ለመምህራን በተደረገ ቃለመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል። በመሆኑም የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን ለሌሎች የተማሪ ተኮር ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴዎችም ትኩረት ቢሰጡ፣
- የመንግስት ትምህርት ቤቶችን የመማሪያ ክፍሎች በሮች፣ መስኮቶች፣ ወለልና ግድግዳ ወዘተ አጠቃላይ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልክ ለመተግበር በሚያስችል ሁኔታ እድሳት ቢደረግላቸው፣
- የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የክፍል ተግባራትን በሚሰጡበት ጊዜ ልክ እንደ ግል ትምህርት ቤቶች መምህራን በማግባባትና ስምምነት በመፍጠር መልክ ቢተገበሩ፣
- የመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን ተማሪዎችን በማቅረብና በማበረታታት በንቃት እንዲሳተፉ የማድረግ ስራ ቢሰሩ፣
- የግል ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች የመማሪያ መጻሕፍትን በቀላሉ ማዳረስ የሚችሉበትን መንገድ ቢያመቻቹ፣
- በተለይም የአንዱ የግል ትምህርት ቤት አስተዳደርና መምህራን በመተባበር የተማሪ ተኮር ትግበራን ጠቀሜታ ለተማሪዎች በግልጽ ማሳወቅ (ስልጠና መስጠት) ቢችሉ፣
- የመንግስትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የእያንዳንዱን የማስተማሪያ ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተረድተው የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ቢያመቻቹ፣

## ዋቢ ጽሑፎች


ለማ ሰጠኝ (1998) "የተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ" በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ አስተባባሪነት ለተዘጋጀ የትምህርት ባለሙያዎች ወርክሾፕ የተዘጋጀ።" አዲስ አበባ (ያልታተመ)።

ሙሉጌታ ይታየው (1996) "የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ ኮ.ሙ.ት.ኮ በሠርቲፊኬትመርሀ ግብር እንደታየው።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

መለሠ በዳኔ (1988) "የመማር ማስተማር ሂደት ለትምህርት ቤት አመራር ስልጠና የተዘጋጀ ማኑዋል።" አዲስ አበባ (ያልታተመ)።

ማረው ዓለሙ (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚጽፉ ድርሰቶች ንጽጽራዊ ጥናት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማተማር ዘዴ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

በድሩ ከድር (1990) "ተማሪ ተኮር ትምህርትና ስነዘዴው።" ለመምህራንና የትምህርት አመራር ባለሙያዎች ስልጠና የተዘጋጀ መመሪያ (ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴር (1994) "የትምህርት መስፋፋትና ጥራት ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው።" ለመምህራንና ርዕሳነ መምህራን በተዘጋጀ አውደ ጥናት ላይ የቀረበ (ያልታተመ)።

አብዱራህማን መሀመድ (1983) መምሁሩና ስራው፡ አዲስ አባባ፤ት.መ.ማ.ማ. ድርጅት።

አለያስ አድማሱ (1997) "በአርሚያ መምህራን ኮሌጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ (2001) የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ደረጀ ነጋሽ (1999) "የተማሪ ተኮር አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ትምህርት ክፍል በ10+3 የስልጠና መርሀ ግብር።" ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ደባሱ አስረስ (1990) "የማሰልጠኛ ዘዴዎች የስልጠና ማንዋል" የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ስልጠና መምሪያ።" አዲስ አበባ (ያልታተመ)።

Aggrawal, J. (1996) *Principles, Methods and Techniques of Teaching.* Delhi: Vikas Publishing House.

Amenu Oljirra (2005) "The Implementation of Active Learning Approach in the Teachers' Colleges of Oromia Region." Addis Ababa University MA Thesis (Unpublished).

Borich, G.D. (1988) *Effective Teaching Methods.* New York: Macmillan Publishing Company.

Brendes, A. (1999) *Collaborative Action Research for English Language Teachers.* Cambridge: Cambridge University Press.

Byrne, Donn (1992) *Techniques for Classroom Interaction.* London: Longman.

Candy, P.C. (1991) *Self-direction for life Long Learning: A Comprehensive Guide to Theory and Practice.* Sanfrancisco: Jossy-Boss, Inc.

Crokes, G and C. Chavdron (1991) "Guide lines for classroom Language Teaching" In M. Celce. Murcia (ed). *Teaching English as a Second or Foreign Language.* Boston Mauss: Heinle and Heinle.

Shank, Cruick (1999) *The Act of Teaching.* Boston: McGraw Hill Companies, Inc.

Doff, A. (1988) *Teaching English: A Training Course for Teachers.* London: Cambridge University Press.

Farrant, J.S. (1980) *Principles and Practice of Education.* New Edition. Long man: Longman Group Ltd.

Fisseha Abreha (2001) "Hampering Factors to Implement Active Learning in some Selected Second Cycle Primary School of Central Zone in Tigray."MA Thesis Addis Ababa University school of Graduate Studies (unpublished).

Gibbs, G. (1981) *Teaching Students to Learning a Student Centered Approach*. Milton Kenes: The Open University Press.

Harmer, J. (1998) *The Practice of English Language Teaching*. London: Longman.

ICDR. (1999 ) *Teacher Education Hand book*. Addis Ababa: Ourael Press.

Knowles, M.S.(1975) *Self-Directed Learning: A Guide for Learners and Teachers*. Engle wood Cliffs: Prentice Hall Regents.

Larmer,G.etal.(1978) "English Teachers use of Student Centered Approach" *Journal of Teaching English Education*.Vol9. No2. pp 111-116.

Leu, E. (2000) "The New Curriculum Issue of Theory and Practice for Teacher Education". Abbiy Addi Collage of Teacher Education BESO Project (Unpublished).

__________ (1988) "Under Standing the Concept of Curriculum. The Basis of Improving Quality." BESO, Project Addis Ababa, Ethiopia. (Unpublished).

Light and Roycox, Greg (2001) *Learning and Teaching in Higher Education*. London: Paulchman Publishing.

Long, M.H. and P.A Porter (1985) "Group Work. Inter Language Talk, and Second Language Acquisitions " *TESOL Quarterly* Vol-19. No. 2:pp. 207-25.

Mc Greal, R. (1988) "Group with Large Classes" *English Teaching Forum*. Vol 27, No. 1 Pp 19-21.

MC Combs, B.L., Whisler J.S. (1997) *The Learner Centered Classroom and School Strategies for Increasing Student Motivation and Achievement*. Sanfrancisco: Jossey Bas Publishers.

Melese Bedane (1999) "Active Learning: Nations, Methods and Examples", Paper Presented on Work Shop in Oromia Education Bureau (Unpublished).

Moore, K. (2001) *Classroom Teaching Skill.* New York: McGraw-Hill.

Mukalel, J. (1998) *Creative Approaches to Classroom Teaching.* New York: Macmillon.

Nachmias, D. and Nachmias, C. (1987) *Research Methods in the Social Sciences.USA:* St, Martin's Press, Inc.

Nunan, D. (1988) *Learner Centered Curriculum.* Cambridge: Cambridge University Press

Opwis, K, and Spada. J. (1994) "*Problem Solving and Learning Computer Modeling*" *the International Encyclopedia of Education.*2nd ed. Vol.8 Elsevier Science Inc.

Plass, H. (1998) "The Learner Centered Classroom" *Quality of Education: in Ethiopia Vision for the 21st Century.* Institute of Educational Research. Addis Ababa University Press.

Reed, A.J. and V.E Bergemann (1995) *In the Classroom: An Introduction to Education.* (2nd ed.) North Carolina Asheville: DPGINC.

Rogers Graham (2002) *Student Centered Learning A Practice Guide for Teachers.* Bangkok: British Council.

Silberman, M. (1994) *Active Learning: 101 Strategies to Teach any Subject.* Boston: Allyn and Bacon

Sirak Demelash (2000) "Learner Centered Instruction in Teacher Training Institutes of Amhara Region." MA Thesis: Addis Ababa University School of Graduate Studies (Unpublished).

Smith, R. (2004) "Project Work" http//www. teaching English org. uk/think/methodology/project.workhtml. accessed 08/08/2010, 5:29.

Temechegn Engida. (2002). "Teaching Primary School Subjects Using Learner Centered Methodology". *The Ethiopia Journal of Educational Researchers Association.* Vol, 1 No 1:pp31-45.

Terefe Tize. (2005). "Practice of Learner Centered Instruction in Debre Markos College of Teacher Education." Addis Ababa University, School of Graduate Studies, MA Thesis (Unpublished).

Tilka, Ananda. S. (1988). "A Learner Centered Report Writing Program" MARA Institute of Technology" Malaysia *English Teaching Forum* Vol. XXVI NP. 2 PP. 9-12

Tsegaye Obssie. 2001. "Learner Centered Approach in Large Classes: A Survey in 13 Selected First cycle Primary Schools in Gedeo Zone /SNNP." MA Thesis: Addis Ababa University (Unpublished).

Tudor. I. (1996). *Learner Centeredness as Language Education.* Cambridge: Cambridge University Press.

Walkin, L. 1989. *Instructional Techniques and Practices.* Chelten ham; ELBS.

Wasihun Derese. (2006). "The Implementation of Student Centered Method of Teaching in Secondary Schools of Mensibu Woreda." Addis Ababa University School of Graduate Studies, MA thesis (unpublished).

Yalew Endawok. (2004). "Teachers Beliefs, Knowledge and Practice of Lerner-centered Approach in Schools of Ethiopia." *The Ethiopian Journal of Education*, Vol.xxiv No. 2 pp. 17-39.

58

## ሙዳዩ ቃላት

| | | |
|---|---|---|
| የሰንጠረዥ ዋጋ | ______ | Critical Value of t |
| ምጋቤ ምላሽ | ______ | Feed back |
| የነፃነት ደረጃ | ______ | Level of freedom |
| አማካይ | ______ | Mean |
| ተነሳስኦት | ______ | Motivation |
| የቲ· ቴስት ውጤት | ______ | Obtained value of t |
| አመች ናሙና | ______ | Convenience sampling |
| ዓላማዊ ናሙና | ______ | Purposive sampling |
| ጠቅላይ ናሙና | ______ | Comprehensive Sampling |
| አስተማማኝነት | ______ | Reliability |
| ልይይት | ______ | Variance |
| የጉልህነት ደረጃ | ______ | Level of significance |
| የስህተት ይሁንታ | ______ | Probability of error |
| ግብዓት | ______ | Input |
| መተግበር | ______ | Executed |
| ማቀድ | ______ | Conceived |
| የተግባራት ቅደም ተከተል | ______ | Actions sequence |
| የተደራጀ ምልከታ | ______ | Structured observation |
| ሚና ጨዋታ | ______ | Role play |
| ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ | ______ | Problem solving approach |
| አይነታዊ ምርምር | ______ | Qualitative Research |
| መጠናዊ ምርምር | ______ | Quantitative Research |

ከበረወች

## አባሪ 1፡-ሥራ ላይ የዋሉ የቲ-ቴስት ስሌት ቀመሮች

$DF = (n_1-1) + (n2-1)$ or $(n_1+n_2)-2$ $= (2+2) - 2 = 2$ and $(88+37)-2 = 123$

$$S^2 = \frac{\Sigma (Xi-X)^2}{n-1}$$

$$= \frac{(4-4.125)^2 + (4.25-4.125)^2}{2-1}$$

$$= \frac{(-0.125)^2 + (0.125)^2}{1}$$

$$= 0.016 + 0.016$$

$$= 0.032$$

$$t = \frac{X_1 - X_2}{\sqrt{\frac{S_1^2 + S_2^2}{n}}}$$

$$= \frac{4.125 - 4.375}{\sqrt{\frac{0.032+0.032}{2}}}$$

$$= \frac{0.25}{\sqrt{\frac{0.064}{2}}}$$

$$= \frac{0.25}{\sqrt{0.032}}$$

$$= \frac{0.25}{0.179}$$

$$= 1.397$$

$$t = \frac{X_1 - X_2}{\sqrt{\left[\frac{(n_1-1)S_1^2 + (n_2-1)\ S_2^2}{(n_1+n_2) - 2}\right](1/n_1+1/n_2)}}$$

$$= \frac{4.364 - 4.458}{\sqrt{\left[\frac{(88-1)0.004 + (37-1)\,0.198}{(88+37)-2}\right](1/88 + 1/37)}}$$

$$= \frac{0.094}{\sqrt{\left[\frac{(87)\,0.004 + (36)\,0.198}{125-2}\right](0.011 + 0.027)}}$$

$$= \frac{0.094}{\sqrt{\frac{(0.348 + 7.128)\,(0.038)}{123}}}$$

$$= \frac{0.094}{\sqrt{\frac{(7.476)\,(0.038)}{123}}}$$

$$= \frac{0.094}{\sqrt{\frac{0.284}{123}}}$$

$$= \frac{0.094}{\sqrt{0.002}}$$

$$= \frac{0.094}{1.519}$$

$$= \underline{0.062}$$

X= Mean

$S^2$= Variance

$S_1^2$= Variance of $n_1$

n= Number of Students/Teachers

DF= Degree of freedom

$X_1$= Mean of the first group

$X_2$= Mean of the second group

$S_2^2$= Variance of $n_2$

t= Critical value of t

## አባሪ 2፡-በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

ከመንግስትና ከግል ትምህርት ቤቶች በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ።

1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| የመምህራን መለያ ኮድ | ጥያቄ 1 | ጥያቄ 2 | ጥያቄ 3 | ጥየቄ 4 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 4.00 | 4.00 | 2.4 | 4.00 |
| 02 | 4.25 | 3.75 | 2.2 | 4.00 |
| አማካይ | 4.125 | 3.875 | 2.3 | 4.00 |
| 03 | 4.5 | 4.25 | 2.2 | 4.333 |
| 04 | 4.25 | 4.00 | 2.2 | 4.00 |
| አማካይ | 4.375 | 4.125 | 2.2 | 4.167 |

2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| የመምህራን መለያ ኮድ | ጥያቄ 1 | ጥያቄ 2 | ጥያቄ 3 | ጥየቄ 4 | ጥየቄ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 4.324 | 4.062 | 3.086 | 4.273 | 4.409 |
| 02 | 4.404 | 3.813 | 3.214 | 4.603 | 3.364 |
| አማካይ | 4.364 | 3.938 | 3.15 | 4.438 | 3.887 |
| 03 | 4.772 | 4.402 | 3.756 | 4.848 | 4.609 |
| 04 | 4.143 | 4.089 | 3.229 | 4.429 | 4.214 |
| አማካይ | 4.458 | 4.246 | 3.493 | 4.639 | 4.412 |

## አባሪ 3፡- የምልከታ ማመሳከሪያ ሰነድ /ቅጽ/

መግቢያ፡- የዚህ የክፍል ውስጥ ምልከታ ዋና ዓላማ በደብረታቦር ከተማ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶችን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበርን መፈተሽ ነው።

1. የትምህርት ቤቱ ስም ______________________
2. ምልከታ የተደረገበት "ሴክሽን" ______________________
3. ምልከታው የተደረገበት ቀን ______________________
4. የክፍል ጊዜ ርዝማኔ ______________________
5. በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ብዛት ______________________
6. ትምህርቱ የተጀመረበት ሰዓት ______________________
7. ትምህርቱ የተጠናቀቀበት ሰዓት ______________________

መግለጫ፡- ለምልከታ በተዘጋጀው ቅፅ ከ1-2 ምርጫዎች የተቀመጡ ሲሆን፡-

2. አዎ (ተተግብሯል)
1. የለም (አልተተገበረም) የሚለውን ውክልና የያዙ ናቸው።

| ተ ቁ | የምልከታ መከታተያ ጥያቄዎች | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ በትምህርቱ መግቢያ<br>1.1. የማነቃቂያ ጥያቄዎችን /መንደርደሪያ ሀሳቦችን/ ያቀርባሉ? | | |
| | 1.2. የእለቱን ትምህርት አላማ ለተማሪዎች በግልጽ ያስተዋውቃሉ? | | |
| | 1.3 የቤትና የክፍል ስራዎች ተከታትለው ምጋቤ ምላሽ /Feed back/ ይሰጣሉ? | | |
| | 1.4. ትምህርቱን ከተማሪዎች የእለት ከዕለት ተግባር ጋር አዛምደው ያቀርባሉ? | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ በትምህርቱ ሂደት<br>2.1. ተማሪዎችን እንዲጠይቁና እንዲመልሱ ያበረታታሉ? | | |
| | 2.2. በቡድን ማስተማር ጊዜ ተማሪዎችን በፆታና በችሎታ አሰባጥረው ይመድባሉ? | | |
| | 2.3. በቡድን ማስተማር ጊዜ የቡድን መሪ ያስመርጣሉ? | | |
| | 2.4. የግልም ሆነ የቡድን ሥራ በሚሰጡበት ጊዜ በተማሪዎች መካከል እየተዘዋወሩ ድጋፍ ያደርጋሉ? | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ የስነ ዘዴ አተገባበር<br>3.1. በግል የማስተማር ዘዴን ይጠቀማሉ? | | |
| | 3.2. የቡድን ማስተማር ዘዴን ይተገብራሉ? | | |
| | 3.3. በፕሮጀክት የማስተማር ዘዴ ያስተምራሉ? | | |
| | 3.4. ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ? | | |
| | 3.5. በሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴ ያስተምራሉ? | | |
| 4 | በማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ<br>4.1. ጥያቄ መጠየቅ፣ መመለስና ሃሳባቸውን በነፃነት መናገር ይችላሉ? | | |
| | 4.2. ለንግግር፣ ክርክር ወይም ውይይት የሚጋብዙ ርዕስ ጉዳዮችን መርጠው ክርክር፣ ንግግር ወይም ውይይት ያደርጋሉ? | | |
| | 4.3. የክፍልና የቤት ሥራዎችን በቃል ወይም በጽሑፍ ክፍል ውስጥ ያቀርባለ? | | |
| 5. | የትምህርት ቤቱ አካባቢና የመማሪያ ክፍሉን ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው አመችነት<br>5.1. የትምህርት ቤቱ አካባቢ ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ነው? | | |
| | 5.2. የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትግበራ የተሟላ ነው? | | |

የተሰየ ካለ ______________________________

አባሪ 4፦ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## በቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ
## የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት
## የድህረ ምረቃ መርሐግብር

በደብረታቦር ከተማ በሚገኙ 2 የግልና 2 የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር ፍተሻን አስመልክቶ ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ።

ውድ ተማሪዎች፦

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በደብረታቦር ከተማ በ2 የግልና በ2 የመንግስት ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪ ተኮር ዘዴ አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት በሚል ርዕስ 8ኛ ክፍልን ተተኳሪ በማድረግ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ለጥናቱ መሳካት መልካም ትብብር እንድታደርጉልኝ ስል በትህትና እጠይቃለሁ።

በቅድሚያ ውድ ጊዜያችሁን ተጠቅማችሁ ስላደረጋችሁልኝ ትብብር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

አጥኚዋ

ማሳሰቢያ፦ በመጠይቁ ላይ ስም፣ ክፍል፣ ቁጥር የመሳሰሉትን መፃፍ አያስፈልግም።

- ግልፅ ያልሆነልህ/ሽ ጥያቄ ካለ መጠይቁን የሚያስሞላውን አካል መጠየቅ ይቻላል።
- የምትሰጠው/ዪው መረጃ ከዚህ ጥናት ውጭ ለምንም ተግባር አይውልም።
- ከሌላ ተማሪ ጋር ተባብሮ መስራት አይፈቀድም።

አጠቃላይ መመሪያ

ይህ የጽሑፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች አሉት። አንደኛው ክፍል አምስት አማራጮችን የያዘ የምርጫ ጥያቄ ነው። ስለሆነም ትክክል ነው ከምትለው/ዪው አንዱን ብቻ በመምረጥ በመረጥከው/ሽው ቁጥር ትይዩ የ/ ✓ / ምልክት አድርግ/ጊ።

አማራጭ መልሶች፡-

5. ዘወትር ይተገበራል
4. አልፎ አልፎ ይተገበራል
3. ለመወሰን እቸገራለሁ
2. አልፎ አልፎ አይተገበርም
1. ፈፅሞ አይተገበርም

በሶስተኛው ክፍል የተዘጋጁት ጥያቄዎች ደግሞ ክፍት ሆነው አጭርና ግልፅ መልሶችን የሚፈልጉ ናቸው። በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ያለህን/ሽን ሀሳብ ከመግለፅ ወደ ኋላ እንዳትል/ዪ ስል አደራዬ ጥብቅ ነው።

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ መረጃ

ተገቢ ለቀረቡት ጥያቄዎች የምትስማማበትን/ሚበትን የ"✓" ምልክት በማድረግ መልስ/ሽ

1. የምትማር/ሪበት ትምህርት ቤት ስም ______________________
2. ፆታ ሀ. ወንድ☐
   ለ. ሴት ☐
3. እድሜ 13-16☐
   17-20 ☐
   ከ 21-በላይ☐

## ክፍል ሁለት

የሚከተሉትን ሀሳቦች ካነበብክ/ሽ በኋላ ከቀረቡት አማራጮች በ አንዱ ስር "✓" ምልክት በማድረግ መልስ/ሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5. | 4. | 3. | 2 | 1. |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ በትምህርቱ መግቢያ<br>1.1. የሚከታተያ ጥያቄዎችን /መንደርደሪያ ሀሳቦችን/ ያቀርባሉ? | | | | | |
| | 1.2 የእለቱን ትምህርት አላማ ለተማሪዎች በግልጽ ያስተዋውቃሉ? | | | | | |
| | 1.3 የቤትና የክፍል ስራዎች ተከታትለው ምጋቤ ምላሽ /Feed back/ ይሰጣሉ? | | | | | |
| | 1.4. ትምህርቱን ከተማሪዎች የእለት ከዕለት ተግባር ጋር አዛምደው ያቀርባሉ? | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ በትምህርቱ ሂደት<br>2.1. ተማሪዎችን እንዲጠይቁና እንዲመልሱ ያበረታታሉ? | | | | | |
| | 2.2. በውይይት ማስተማር ጊዜ ተማሪዎችን በፆታና በችሎታ አሰባጥረው ይመድባሉ? | | | | | |
| | 2.3. በውይይት ማስተማር ጊዜ የውይይት መሪ ያስመርጣሉ? | | | | | |
| | 2.4. የግልም ሆነ የውይይት ሥራ በሚሰጡበት ጊዜ በተማሪዎች መሀል እየተዘዋወሩ ድጋፍ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ/ሯ የስነ ዘዴ አተገባበር<br>3.1. በግል የማስተማር ዘዴን ይጠቀማሉ? | | | | | |
| | 3.2. የውይይት ማስተማር ዘዴን ይተገብራሉ? | | | | | |
| | 3.3. በፕሮጀክት የማስተማር ዘዴ ያስተምራሉ? | | | | | |
| | 3.4. ችግር ፈቺ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ? | | | | | |
| | 3.5. በሚና ጨዋታ የማስተማር ዘዴ ያስተምራሉ? | | | | | |
| 4 | በማርኛ ቋንቋ ክፍል ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ<br>4.1. ጥያቄ መጠየቅ፣ መመለስና ሃሳባችሁን በነፃነት መናገር ትችላላችሁ? | | | | | |
| | 4.2. ለንግግር፣ ክርክር ወይም ውይይት የሚጋብዙ ርዕስ ጉዳዮችን መርጣችሁ ክርክር፣ ንግግር ወይም ውይይት ታደርጋላችሁ? | | | | | |
| | 4.3. የክፍልና የቤት ሥራዎችን በቃል ወይም በጽሑፍ ክፍል ውስጥ ታቀርባላችሁ? | | | | | |
| 5 | የትምህርት ቤቱ አሰባቢና የመማሪያ ክፍሉን ለተማሪ ተኮር ትምህርት ትግበራ ያለው አመችነት<br>5.1. የትምህርት ቤቱ አሰባቢ ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ነው? | | | | | |
| | 5.2. የመማሪያ ክፍሉ ለተማሪ ተኮር ትግበራ የተመቻ ነው? | | | | | |

68

## ክፍል ሶስት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ልቅ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ፃፍ/ፊ።

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሩ ምን ምን ይሰራሉ?

2. በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስትማር/ሪ ያጋጠሙህ/ሽ ችግሮች አሉ? ካሉ ችግሮቹን በዝርዝር ፃፍ/ፊ።

3. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ሂደትን በተመለከተ መደረግ ወይም መሟላት አለበት የምትለው/ዪው አስተያየት ካለህ/ሽ በዝርዝር አስፍር/ሪ

መጠይቁን ሞልተህ/ሽ በመመለስ ላደረግህልኝ/ሽልኝ ቀና ትብብር በድጋሚ አመሰግናለሁ።

አጥኝዋ

ህዳር 2003 ዓ.ም

## አባሪ 5፦ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
### በቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ
### የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት
### የድህረ ምረቃ መርሐግብር

በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን በደብረታቦር ከተማ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች 8ኛ ክፍልን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

- እድሜ________________________
- ፆታ ________________________
- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም________________________
- የትምህርት ደረጃ ________________________
- የአገልግሎት ዘመን ________________________
- በአብይ የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ________________________

70

መሪ ጥያቄዎች

1. ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወስደው ከሆነ መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ቢገልፁልኝ?
2. የአማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩበት ጊዜ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ይጠቀማሉ?
3. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ሲተገብሩ በብዛት የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ?
4. ተማሪዎችን በቡድን የሚያደራጁት ምንን መሠረት በማድረግ ነው? የአንድ ቡድን አባላትስ ከስንት እስከ ስንት ቢሆን ጥሩ ነው ይላሉ?
5. በቡድን ውይይት ወቅት የእርስዎና የተማሪዎች ሚና ምን ምን ናቸው?
6. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?
7. በትምህርት ቤቱ የተማሪ ተኮር ትምህርት በአግባቡ እንዳይተገበር እንቅፋት ሆኗል የሚሉት ነገር ካለ ቢገልፁልኝ? መፍትሔውስ ምን ሊሆን ይችላል ብለው ያምናሉ?
8. በአጠቃላይ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ያለዎትን አመለካከት ዘርዝር አድርገው ቢገልፁልኝ?

## አባሪ 6፦ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን - 06/04/2003
ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት - 7:30-8:30
ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቦታ -ዳግማዊ ቴዎድሮስ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

መምህር -01

ዕድሜ - 47

ፆታ - ሴ

የትምህርት ደረጃ -ዲግሪ

የአገልግሎት ዘመን- 28

በአብይ የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ - አማርኛ

ጥያቄ 1. ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወስደው ከሆነ መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ቢገልጹልኝ?

መልስ፦ በትምህርት ቤታችን የጉድኝት ማዕከል ለ3 ጊዜ ያህል በራሳችን የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን በርዕስነት በማንሳት ባለሙያ እየተጋበዘ ለአንድ ለአንድ ቀን በስልጠና መልክ ወስጃለሁ።

ጥያቄ 2. የአማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩበት ጊዜ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ይጠቀማሉ?

መልስ፦ ብዙ ጊዜ አልተረጉመውም። ምክንያቱም የተማሪ ቁጥር ብዛት በመኖሩ የተማሪ ተኮር ትምህርትን በአግባቡ ለመተግበርና ሁሉንም ተማሪዎች ለማሳተፍ አይቻልም።

ጥያቄ 3. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ሲተገብሩ በብዛት የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ?

መልስ፦ በአብዛኛው የግልና የቡድን ስራን ተግባራዊ ሲደረጉ ሌሎቹ ግን ተግባራዊ እየተደረጉ አይደለም ማለት ይቻላል።

**ይቀጥላል**

ጠያቂ- እመስግናለሁ

መልስ- ምንም አይደል

ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን - 08/04/2003

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት - 5:30-6:15

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቦታ - ፊታ እውራሪ ገብር 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

መምህር -02

ዕድሜ - 48

ፆታ - ወንድ

የትምህርት ደረጃ - ዲግሪ

የአገልግሉት ዘመን- 28

በአብይ የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ - አማርኛ

ጥያቄ 1. ስለተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወስደው ከሆነ መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ቢገልጹልኝ?

መልስ፡- አዎ ወስጀ አውቃለሁ፤ ለሶስት ጊዜ ያህል የአንድ አንድ ቀን ስልጠና በትምህርት ቤታችን በጉድኝት ማዕከላችን አማካኝነት ሰልጥኛለሁ፡፡

ጥያቄ 2. የአማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩት ጊዜ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ይጠቀማሉ?

መልስ፡- እንደ አስፈላጊነቱ እጠቀማለሁ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የማልጠቀምበት ወቅት አለ።

ጥያቄ 3. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ሲተገብሩ አዘውትረው /በብዛት/ የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ?

መልስ፡- የተለያዩ ተግባራትን በግል ከሠሩ በኋላ በቡድን እዲያዳብሯቸው የማድረግ ሂደት እጠቀማለሁ። ከዚህ ውጭ ግን አልጠቀምም፡፡

ይቀጥላል

ጠያቂ- አመሰግናለሁ

መልስ- ምንም አይደል

ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን - 04/04/2003

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት - 8:30-9:15

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቦታ - ዲቲ አካዳሚ ትምህርት ቤት

መምህር -03

ዕድሜ - 23

ፆታ - ወንድ

የትምህርት ደረጃ - ዲግሪ

የአገልግሎት ዘመን- 4 ዓመት

በአብይ የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ-እንግሊዝኛ

ጥያቄ 1. ስለተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወስደው ያውቁ ከሆነ መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ቢገልጹልኝ?

መልስ፦ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ወስጃለሁ፤ በስራ አለም ግን ምንም አይነት የስልጠና እድሉ አልገጠመኝም።

ጥያቄ 2. የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚያስተምሩበት ጊዜ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ይጠቀማሉ?

መልስ፦ አዎ

ጥያቄ 3. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ በብዛት የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ?

መልስ፦ ብዙ ጊዜ በራስ የመማር ዘዴና በቡድን የማስተማር ዘዴን እጠቀማለሁ።

.

.

.

ይቀጥላል

ጠያቂ፦ አመሰግናለሁ

መልስ፦ ምንም አይደል

ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን - 08/04/2003

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት - 7:30-8:30

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቦታ - ዳልሽህ ቤዛዊት አለም ትምህርት ቤት

መምህር -04

ዕድሜ - 23

ፆታ - ወንድ

የትምህርት ደረጃ - ዲግሪ

የአገልግሎት ዘመን- 1 ዓመት

በአብይ የሰለጠኑበት የትምህርት መስኩ-አማርኛ

ጥያቄ 1. ስለ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ? ወስደው ከሆነ መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ቢገልጹልኝ

መልስ፡- አዎ በዩንቨርስቲ ደረጃ በ "subject area course" አማካኝት ለ1 ሴሚስተር ያህል ወስጃለሁ ወደ ስራ አለም ከገባሁ ግን ምንም ዓይነት ስልጠና አልወሰድኩም፡፡

ጥያቄ 2. የአማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩበት ጊዜ የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን ይጠቀማሉ?

መልስ፡- ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን ለተማሪዎች ማስታወሻ በማስያዝ በማስታወሻነት የያዙትን ደግሞ በማስረዳት ግልፅ እንዲሆንላቸው ለማድረግ የገለፃ ስልትን እጠቀማለሁ፡፡

ጥያቄ 3. የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብን በሚተገብሩበት ጊዜ አዘውትረው የሚጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ?

መልስ፡- በአብዛኛው በግል (በራሳቸው) እንዲሰሩ በማድረግ ከዚያም ሁለትና ከሁለት በላይ ሆነው በጋራ እንዲወያዩ አደርጋለሁ፡፡

.

.

.

ይቀጥላል

ጠያቂ- አመሰግናለሁ

መልስ- ምንም አይደል

## አባሪ 7፡-፡-ከምልከታና ቪዲዮ ቀረጻ የተገኘ መረጃ

በዳግማዊ ቴዎድሮስ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ምልከታና የቪዲዮ ቀረጻ

ቀን 29/03/2003 ዓ.ም

ሰዓት 6፡30-710

75

የዳግማዊ ቴዎድሮስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለትምህርት አመች የሆነ አካባቢ ላይ የተመሰረተ ነው። የመማሪያ ክፍሎች ሁሉ በጥሩ ሁኔታ የተገነቡ ናቸው።

የክፍሉ መምህርና ምልከታውን የምናካሂደው እንግዶች በ6፡30 ላይ ነበር ወደ 8ኛ C ክፍል የገባነው።ተማሪዎች ከመቀመጫቸው ተነስተው እንግዶቹንና መምህራናቸውን የተቀበሉን እኛም ሠላምታ ሰጥተናቸው ተቀመጥን። የ8ኛ "C" ክፍል ከትምህርት ቤቱ በብሎኬት ከተገነቡት የመማሪያ ክፍሎች መካከል አንዱ ነው። ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ መቀመጫ ወንበሮች "ዴስኮች"ና በቂ የፀሀይ ብርሃን የሚያስገቡና በአረንጓዴ ቀለም የተቀቡ የመስታወት መስኮቶች የተገጠመለት፣ወለሉ ስሚንቶ ና ንፅህናው የተጠበቀ፣ ጥቁር ሰሌዳ ያለው ሲሆን በር ግን አልተገጠመለትም። በሌላ በኩል ደግሞ የተማሪዎችን አቀማመጥ በምናይበት ጊዜ ከተለመደው አቀማመጥ ለየት ያለ ነበር። ይህም ከሁለት ወይም ከሶስት ዴስኮች ያሉ ተማሪዎች ፊት ለፊት ወይም "የፈረስ ኩቴ" አይነት አቀማመጥ ተቀምጠው ይስተዋላሉ። በመሆኑም መምህሯ ገለፃ በሚያደርጉበትና ከጥቁር ሰሌዳው ላይ የተለያየ ማስታወሻዎችን በሚፅፉበት ጊዜ ወደ ሰሌዳው ወይም መምህሯ አቅጣጫ ለመዞር ተማሪዎች የመጠማዘዝና ምቾት የማጣት ስሜት ይታይባቸዋል። መምህሯ ከጥቁር ሰሌዳው ማዕከል ወደ ላይ ከፍ ብለው የእለቱን ትምህርት "የንግግር አይነቶች" የሚል ርዕስና ዓላማ በመፃፍ ያለፈውን ትምህርት የሚያስታውሰኝ ማን ነው? ሲሉ ጠየቁ ተማሪዎች እጃቸውን በማውጣት ስለ ውይይትና ቃለ ጉባኤ አያያዝ "ተምረን በተሰጠን ርዕስ እየተወያየን ሳለ ሰዓት ስለደረሰብን የተሰጠንን ጥየቄ በቤት ስራ መልክ ሰርተን መጥተናል።

ይቀጥላል

በፊታአውራሪ ገብርየ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ምልከታና የቪዲዮ ቀረፃ

ቀን 27/03/2003

ሰዓት 3፡20-4፡00

የፊታ አውራሪ ገብርየ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደልዳላና ሀጥታ የሰፈነበት ቦታ ላይ ነው የቆረቆረው። በርቀት ሲያዩት የትምህርት ቤቶች ክፍሎች የጭቃ ግድግዳና የማረቱ የጣራ ቆርቆሮዎች መሆናቸው በግልፅ ይታያል። በእለቱ 3፡20 ላይ ነበር እንደግዶችና የክፍል መምህሩ ወደ "8ኛ A ክፍል የገባነው። በዚህ ጊዜም ተማሪዎች ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀበሉን ከተማሪዎች ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እንዲቀመጡ በማድረግ የእለቱን እንግዶችም ከተማሪዎች ጋር ተቀመጥን። የመማሪያ ክፍሉ ግድግዳ የተፋፈቀ ይሁን እንጅ ነጭ ቀለም ተቀብቶ እንደነበር በታሪክ አሻራነት ይስተዋላል። ይህ የመማሪያ ክፍል በስተምስራቅ በኩል 2 ሰፋፊ መስኮቶች ያሉት፤ በሩም የቆርቆሮና ወደ ምዕራብ የዞረ ነው። በመሆኑም ከሰዓት በፊት ፈረቃ የፀሀይ ጮራ በመስኮት በኩል ዘልቆ በመግባት ከተማሪዎች ደብተርና መጽሐፍ ላይ በማረፍ፤ እንዲሁም የከሰዓት ፈረቃ ሲሆን ደግሞ የፀሀይ ጮራ በበሩ በመግባት ያስቸግራል። ይህንን ከልክ ያለፈ የፀሀይ ብርሃን ለመቀነስ በሩን ወይም መስኮቱን ሲዘጉት ደግሞ ወለሉ መሬትና ለአቧራ የተጋለጠ በመሆኑ መምህሩ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አፈር ስለሚነሳ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ሰላም አይሰጥም። ክፍል ውስጥ ያሉ ወንበሮችን በምናይበት ጊዜ ደግሞ "ዴስኮች" ሆነው መደገፊያቸው የተላቀቁ ይበዙበታል። ስለሆነም ተማሪዎች ለመቀመጥም ሆነ ለመነሳት ጥንቃቄ ካላደረጉ የመውደቅ እድል ሊገጥማቸው ይችላል። ይሁን እንጅ በዚህ ክፍል ውስጥ 49 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ይስተናገዳሉ፤ የተማሪዎች አቀማመጥ የአንዱን "ዴስክ" ተማሪ ከሌላው ጋር ፊት ለፊትና የፈረስ ኮቴ አይነት አቀማመጥ ነው። መምህሩ ያለፈውን ትምህርት ተማሪዎች እንዲያስታውሷቸው አደረጉ።

.

.

.

ይቀጥላል

በጫቲ አካዳሚ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ምልከታና የቪዲዮ ቀረፃ

ቀን 24/03/2003 ዓ.ም

ሰዓት 4፡00-4፡40

የጫቲ አካዳሚ ትምህርት ቤት በደልዳላ ቦታ ላይ የተቆረቆረ ስህፃናት ሰፊ ሜዳና የተለያዩ መጫዎቻዎች ያሉት ነው። አካባቢው ፀጥታ የተሞላበትና ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚመች ነው። የክፍሉ ህንጻም የብሉኬት ነው። በእለቱ እንግዶቹና መምህሩ በ4፡00 ነበር ወደ ክፍል የገባነው። ተማሪዎችም ከመቀመጫቸው በመነሳት እንግዶቹንና መምህራቸውን ተቀበሉን እኛም ሆን መምህሩ ሰላምታ ሰጥተናቸው እንዲቀመጡ አደረግን። በክፍሉ ያሉት ተማሪዎች በቁጥር 23 ናቸው። ክፍሉም ጠበብ ያለና ለእነዚህ ተማሪዎች በቂ የሆነ ነው። ወንበሮቹ "ዴስክ" ናቸው ግድግዳውና ወለሉም ንፁህ ነው። በሩ ላሜራና መስኮቶቹ ደግሞ በቂ ብርሃንን የሚያስተላልፍና የመስታወት ናቸው።

መምህሩም ያለፈውን ትምህርት በማስታወስ የቤት ስራ አለን አይደል? በማለት ተማሪዎችን ጠየቁ ተማሪዎችም አለን ሲሉ መለሱላቸው። በዚህ ጊዜም መምህሩ ፈጠን ብለው ደብተራቸውን በማየት ከተማሪዎች ደብተር ላይ ፊርማቸውን አስቀመጡ። በመቀጠልም ከቤት ስራው ውስጥ በትዕዛዝ ሁለት ስር ያሉትን የወተት ተዋጽኦዎች በቅደም ተከተል አስቀመጡ የሚልና እርጎ፣ አይብ፣ ወተት፣ ቅቤ፣ አሬራ (ወገሚት ነበር። ከተማሪዎች አንዱ እጁን አውጥቶ ወተት፣ እርጎ፣ ቅቤ፣ አሬራ (ወገማት)ና አይብ በማለት ቅደም ተከተላቸውን አስተካክሉ ተናገረ። ከዚያም መምህሩ ተማሪውን በማበረታታት ለሌሎች ተማሪዎችም ግልፅ መሆኑን በመጠየቅ ግልጽ መሆኑን አረጋገጡ። በዚህ ሁኔታም ሌሎች በትዕዛዝ አራት ስር ያሉና ተዘበራርቀው የተቀመጡ አባባሎችንም በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ በማድረግ የቤት ስራውን በዚህ ሁኔታ አጠናቀቁ።

.

.

.

ይቀጥላል

በዳልሽሀ ቤዛዊት አለም 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተካሄደ ምልከታና ቪዲዮ ቀረፃ

ቀን 24/03/2003

ሰዓት 8፡30-9፡10

የዳልሽሀ ቤዛዊት አለም ትምህርት ቤት ለመማር ማስተማር ሂደት አመችነት ያለውና ፀጥታ ከሰፈነበት ቦታ ላይ ነው የተቆረቆረው። የክፍል መምህርና ምልከታውን የምናካሂደው እንግዶች በ8፡30 ነበር ወደ ክፍል የገባነው። ተማሪዎችም ከመቀመጫቸው ተነስተው በአክብሮት "Well come gests" በማለት ተቀበሉን በዚህ ጊዜ እኛም ሆን መምህሩ ተማሪዎችን ሰላምታ ሰጥተናቸው እንዲቀመጡ አደረግን። እንግዶቹም ከተማሪዎች ጋር ተቀመጥን። የተማሪዎች አቀማመጥም የተለመደውን አይነት አቀማመጥ ማለትም ወደ ጥቁር ሰሌዳው ዞረው ነበር። የመማሪያ ክፍሉ በብሎኬት የተሠራ ሲሆን በሩ ላሜራ ነው። መስኮቶቹ ደግሞ በቂ ብርሃን የሚያስገቡ የመስታወት ናቸው። ወለሉ ምንም እንኳን ያልተስተካከለና ጉርብጥብጥ ያለ ነበር ቢኖረውም ሊሾና ከአቧራ የፀዳ ነው። በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ወንበሮችም ልክ እንደሌሎች ትምህርት ቤቶች "ዴስኮች" ናቸው። የተማሪዎች ቁጥርም 14 በመሆኑ የክፍሉ ስፋት ከተማሪዎች ብዛት ጋር ሲታይ ተመጣጣኝ አይደለም።

መምህሩም በሰሌዳው ላይ የትምህርት አይነቱንና "በድምጾች ትንጅት የሆሄያት ቅርጽ መለወጥ" በማለት ጻፈ።

.
.
.

ይቀጥላል

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማየን ያስቀመጥኩ የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱ ውስጥም የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎችና ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

79

ስም፡- ሶስና አወቀ

ፊርማ፡- ____________

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ፣ አማርኛ ትምህርት ክፍል።

የማስረከቢያ ጊዜ፡-መጋቢት 2003 ዓ.ም